የአቤቶሁን ፡ ያዕቆብ ፡
ትውልድና ፡ አሟር ፡ ታሪክ ።



ጥንቢት ፡
ያ — ይንበር ።

የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ነገሥት ፡ዘኢትዮጵያ ፡ የኃያኛው ፡ ዓመት ፡
የልደት ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ።

ተጻፈ ፡ ከታደሰ ፡ ዘመልዴ ።



አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም.

በቀርጥንስ ፡ ፅላም ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

የአቤቶሁን ፡ ያዕቆብ ፡ ትውልድና ፡ አጭር ፡ ታሪክ ።



ት ን ቢ ት ፡
ያ — ይነብር ።

የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ነገሥት ፡ዘኢትዮጵያ ፡ የሟቹኛው ፡ ዓመት ፡
የልደት ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ።

ተጻፈ ፡ ከታደሰ ፡ ዘወልዴ ።



አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም.

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ያለ ፡ ደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ማተም ፡ ወይም ፡ መገልበጥ ፡ ክልክል ፡ ነው ፡ ።

ማርማዊ ፡ ሆይ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ከኔ ፡ የቀደሙት፡ብዙዎች፡ሊቃውንት ፡ የጻፉት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የታሪክ ድርሰት፡ቢኖርና ፡ ለወደፊቱም ፡ የሚደረሱ፡ ታላላቅ ፡ ታሪኮች ፡ እንደሚኖሩ ፡ ቢታወቅም ፡ እኔም ፡ በበኩሌ ፡ የታላቁን ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብን ፡ ትውልድና ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ ያነቃቃኝ ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ትውልድና ፡ ከቀደሙት ፡ አበው ፡ እንዱ ፡ ታላቁ ፡ ያዕቆብ ፡ በሕልም ፡ ራእይ ፡ የታየውን ፡ መሰላል ፡ (ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፰) ፡ በማመሳሰል ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ትውልድ ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ መሰላል ፡ ደረጃ ፡ የተከታተሉና ፡ ደንበኛውን ፡ ዘርፍ ፡ ይዘ ፡ ሲወርድ ፡ መጥቶ ፡ እግርማዊነትም ፡ የደረሰ ፡ መሆኑን ፡ ለማስታወስ ፡ ያህል ፡ ያዘጋጀሁትን ፡ ይህን ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ፡ ለግርማዊነትም ፡ ለስድሳ ፡ አራተኛው ፡ ዓመት ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆንልኝ ፡ ዘንድ ፡ ለማርማዊነትም ፡ በታላቅ ፡ ፍርሃት ፡ አበረክታለሁ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፰ ፡ ዓ ም

ባ ሪ ያ ም ፡

ታደሰ ፡ ዘወልዴ ።



ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ።

መ ቅ ድ ም ።

መ ጽ ሐ ት ና ፡ አ ገ ል ግ ሎ ቱ ።

በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ መጽሐት ፡ ማለት ፡ መስተዋት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ መስተዋትም ፡ የሚሠራው ፡ ክሪስታል ፡ ከተባለ ፡ ማዕድናዊ ፡ ባሕርይ ፡ ከለው ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አገልግሎቱ ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚነት ፡ ያለው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የተከበረ ፡ ነው ። አገልግሎቱ ፡ መልክን ፡ ለማየት ፡ ከማስቻሉ ፡ በቀር ፡ በክሪስታል ፡ ባሕርይነቱ ፡ ሰው ፡ የሚጠቀምባቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያዎች ፡ ያስገኛል ። ብርጭቆ ፤ መነጽር ፤ ሣህን ፡ ለመሥራትና ፡ ለማናቸውም ፡ ተሽከርካሪና ፡ በሚንቀሳቀስም ፡ በማይንቀሳቀስም ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ሊሠል ፡ ይችላል ። በሁኑ ፡ ጊዜያችን ፡ የድምፅን ፡ ያህል ፡ ፍጥነት ፡ ላላቸው ፡ ብየር ፡ ለሚበሩ ፡ „ አኤሮፕላኖች „ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ በመሆኑ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አንቀሳቃሽና ፡ ጎደላቸው ፡ ሌላ ፡ መሣሪያ ፡ ቢሆንም ፡ ሰው ፡ የውጭውን ፡ በማስተዋልና ፡ በመለየት ፡ አየር ፡ ሳያስቸግረው ፡ ለ ብር ፡ የሚችለው ፡ በክሪስታል ፡ ርዳታ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ አነስተኛውን ፡ ምሳሌ ፡ በመስጠት ፡ የክሪስታልን ፡ ጥቅም ፡ ገለጽን ።

የመጽሐት ፡ ሁለተኛ ፡ ትርጉሙ ፡ ታሪክን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ ገልጸ ፡ የሚያሳይ ፡ ማናቸውም ፡ ጽሑፍ ፡ ማለት ፡ ነው ። መስተዋት ፡ መልክን ፡ አጣርቶ ፡ እንደሚያሳይ ፡ የታሪክንም ፡ ሆነ ፡ የትውልድን ፡ ዝርዝር ፡ እንደ ፡ መስተዋት ፡ አጉልቶ ፡ ስለሚያሳይ ፡ ነው ።

ለዚሁም ፡ ሁሉ ፡ ማረፊያና ፡ ማኅደሪያ ፡ መጽሐት ፡ ጎብሎ ፡ መሰጠቱ ፡ መጽሐት፡ የጠራና እጅግ ፡ ያማረ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ መጽሐት ፡ ማለት ፡ መስተዋት ፡ ሲሆን ፡ መስተዋት ፡ ሲመለከቡበት ፡ ተመልካቹ ፡ በስተ ፡ ኋላው ፡ ያለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ለማየት ፡ እንደሚችል ፡ መጽሐትም ፡ ታሪክን ፡ እየተከታተልን ፡ ያለፈውን ፡ ልናስታውስበት ፡ የሚቻል ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ታሪክ ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ በመተላለፍ ፡ የቁም ፡ ነገር ፡ ምሬውን ፡ በመጻሕፍትና ፡ ሲመርድ ፡ ሲዋረድ ፡ በሚነገረው ፡ ድምፅ ፡ አማካይነት ፡ ሲተላለፍ ፡ ይኖራል ።

የታሪክ ፡ እልባትና ፡ የታሪክ ፡ አካል ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡት ፡ ሞያቸውን ፡ በመልክም ፡ ተግባር ፡ ፈጽመው ፡ ያለፉት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ሆኑ

የነርሱ ፡ ዘርፍ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሊያስታውሳቸውና ፡ ላስታ
ዋሽ ፡ ሊያስተላልፋቸው ፡ የተገባ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህችን ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ለመ
ግለጽ ፡ ፈቀድሁ ።

መሠረታቲሃ ፡ ውስቶ ፡ አድባር ፡ ቅዱሳን ፡ ለብሔረ ፡ መንዝ ፡ ያበድሮን ፡
እግዚአብሔር ፡ ለእናቅጸ ፡ ጽዮን ፡ እምኵሉ ፡ ተዓይኒሁ ፡ ለውሉደ ፡ ያዕቆብ ፡
የሀገረ ፡ መንዝ ፡ መሠረቶቿ ፡ የተቀደሱ ፡ ነገሥታት ፡ አበቶች ፡ ናቸው ።

እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ታላቅ ፡ በሁርን ፡ በማስነጣቱ ፡ ከሌሎቹ ፡
የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ መኖሪያዎች ፡ ይልቅ ፡ ጽዮን ፡ የምታሰኝ ፡ የመንዝን ፡
ደጅ ፡ መረጠ ።

መንዝ ፡ ጽዮን ።

ስለ ፡ አዜቶውን ፡ ያዕቆብ ፡ ትውልድና ፡ አሟሟር ፡ ታሪክ ።

ትንቢት ።

ገ ፡ ይነግሥ ፡ ፈ ፡ ይመውት ፡ ሚ ፡ ይሠየጥ ፡ ያ ፡ ይነብር ፡ ሥጋ ፡ ይሞታል ፡ መደ ፡ መቃብር ፡ ይወርዳል ፡ ስም ፡ ግን ፡ ከመቃብር ፡ በላይ ፡ ይውላል ።

አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ብቃት ፡ የነበራቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ቅር ፡ እያሰኝም ። ይህም ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡ ከግራኝ ፡ መረራ ፡ በፊት ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ አዜቶ ፡ ያዕቆብን ፡ ትተው ፡ በመጂዳቸውና ፡ ከ1500 ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከተዋጉና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ንጉሣዊ ፡ ተጋድሎ ፡ ከሰለፉ ፡ በኋላ ፡ ጠላታቸው ፡ ግራኝ ፡ ድል ፡ ቢያደርግም ፡ እግዚአብሔር ፡ እጃቸውን ፡ አስልሮ ፡ ለጠላት ፡ ሰይሰጥ ፡ መደ ፡ መንግዱና ፡ መደ ፡ ቀና ፡ መንፈሱ ፡ ብቻ ፡ እየመራ ፡ አቂያቲ ፡ ቸው ፡ በመከከሉ ፡ በሕመማቸው ፡ ምክንያት ፡ የዕድሜያቸውን ፡ ፍጻሜ ፡ አመልክቷቸው ፡ ጥንቱንም ፡ በተሰይ ፡ ያከብሩት ፡ መደነበረው ፡ መደ ፡ ይበረ ፡ ጻም ፡ ገዳም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደው ፡ የአስከሬን ፡ ማረፊያቸውን ፡ ሰማ ድረግ ፡ ቢያዙና ፡ ያትርሱኝ ፡ ምጽዋታቸውን ፡ ለገዳሙ ፡ ቢያበረክቱ ፡ የገ ዳሙ ፡ ጎላፊዎች ፡ የንጉሡን ፡ አስከሬን ፡ በማሳረፋቸው ፡ ጠላት ፡ ይቃወሠ ናል ፡ በሚሉ ፡ ፍርሀት ፡ ተነሥተው ፡ አስከሬናቸውን ፡ ደብረአ ፡ መደሚበል ፡ አገር ፡ መስደው ፡ እዋሽ ፡ ሙስዋ ፡ ደብቀው ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ፍርሀታቸው ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ አስከሬናቸውን ፡ እንደገና ፡ መደ ፡ ጥንቱ ፡ በታው ፡ መደ ፡ ይበረ ፡ ጻም ፡ ገዳም ፡ መወሰኗቸውን ፡ ታሪክ ፡ ያረጋግጣል ።

ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ ትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ ሙሉ ፡ ፍቸውና ፡ ትርጉሜው ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ገ ፡ ይነግሥ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ይነግሥ ፡ (ገላውዴዎስ ፡ ይነግናል ።)
ፈ ፡ ይመውት ፡ ፈቅጦር ፡ ይመውት ፡ (ፈቅጦር ፡ ይሞታል ።)
ሚ ፡ ይሠየጥ ፡ ሚናስ ፡ ይሠየጥ ፡ (ሚናስ ፡ ይሸማል ።)
ያ ፡ ይነብር ፡ ያዕቆብ ፡ ይነብር ፡ (ያዕቆብ ፡ ይኖራል ።)

በዚህ ፡ አንጋፊ ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ ተፈጽሞ ፡ በመታየቱና ፡ ወቅዱ ፡ መልክምነትን ፡ ይዘ ፡ በመገኘቱ ፡ አስደናቂ ፡ ሆኗል ።

እንደዚህም ፡ የአጼ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግልን ፡ በለቢት ፡ እቱጌ ፡ ማርያም ፡ ሥናን ፡ ከቤትዋ ፡ የሚወለድ ፡ ልጅ ፡ መንግሥትዎን ፡ ይገለብጣል ፡ እያሉ ፡

ሉሲምቻቸው ፡ እንደ ፡ ትንቢት ፡ አድርገው ፡ ይንግሩዋቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በብዙ ፡ ይጨነቁበትና ፡ ይጠበቡበት ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

እቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥናም ፡ የተነገራቸው ፡ የትንቢት ፡ ቃል ፡ እንዳይፈጸምባቸው ፡ ምንም ፡ ቢጨነቁበት ፡ የሠጉበትና ፡ የተጨነቁበት ፡ ነገር ፡ በዘመናቸው ፡ ተፈጽሞ ፡ አዩት ። ነገር ፡ ግን ፡ የሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ነው ፡ እንደሚባለው ፡ በንጹሕ ፡ ሕዝብ ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ከመፈጸም ፡ የማያልፍ ፡ በመሆኑ ፡ አቤቶ ፡ ፋሲል ፡ (ገራም) ከዕለ ቃት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከወንድማቸው ፡ ከአቤቶ ፡ ሥግዓ ፡ ቃል ፡ ተለይተው ፡ ወደ ፡ እጮታቸው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አጼ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጐን ደር ፡ ተሸግረው ፡ ሳለ ፡ ለእቴጌይቱ ፡ መድኅኒት ፡ ልቀምስ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ስላሉዋቸው ፡ እቴጌይቱም ፡ ይሠጉበትና ፡ ይጨነቁበት ፡ የነበረውን ፡ በመዘንጋት ፡ ፋሲል ፡ የነጋሢ ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ በገረድ ፡ እጅ ፡ መድኅኒት ፡ ሊቀምስ ፡ አይገባምና ፡ ሐማልማል ፡ ታቅምሰው ፡ ሲሉ ፡ አገዘው ፡ መድኅኒት ፡ የሚቀምሱበት ፡ የተለየ ፡ እልፍኝ ፡ ሰጥተዋቸው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ አቤቶ ፡ ፋሲል ፡ የጉልማሣነት ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ አሸነፋቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ሐመልማል ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተው ፡ ኖሮ ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ (በኋላ) ፡ አቤቶ ፡ ልሳነ ፡ ክርስቶስ ፡ ተወለዱ ። ይህም ፡ ሊታወቅ ፡ የተቻለው ፡ በሦስት ፡ መረ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እቴጌይቱ ፡ ያ ፡ ንግር ፡ ትዝ ፡ ቢላቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ሐመልማልን ፡ አጥብቀው ፡ ጠየቋቸው ። ወይዘሮ ፡ ሐመልማል ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ ክዱ ። እቴጌይቱም ፡ ጊዜ ፡ ይግለጠው ፡ ብለው ፡ ሲጠባበቁ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሲሞላቸው ፡ ፅንሱ ፡ እየገፋ ፡ ሄዶ ፡ በመታወቁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥቃይ ፡ በማሳየት ፡ ቢመረምሩዋቸው ፡ ከአቤቶ ፡ ፋሲል ፡ መሆኑን ፡ ከገለጡላቸው ፡ በኋላ ፡ በሙቅ ፡ ውሃ ፡ የጭድ ፡ እብቅ ፡ ጨምረው ፡ ሆዳቸውን ፡ አሳሹዋቸው ፡ ይባላል ። ይህን ፡ ማድረጋቸው ፡ የሚወለደው ፡ ሕፃን ፡ ወይኔ ፡ ስመር ፡ ሆኖ ፡ እንዲወለድና ፡ እንዳይኔ ፡ ሥ ፡ ያቀዱት ፡ ዘዴ ፡ ነበር ። ወይዘሮ ፡ ሐመልማል ፡ የደረሰባቸውን ፡ ሁሉ ፡ ጐሻም ፡ ለንበሩት ፡ ወንድሞቻቸው ፡ በመላክተኛ ፡ ነግረው ፡ ኖሮ ፡ በማሥጋጌ ፡ ደርሰውላቸው ፡ ደብቀው ፡ ወሰዱዋቸው ፡ ይባላል ። አቤቶ ፡ ፋሲልንም ፡ በጥብቅ ፡ ቢያስፈልጉ ፡ አላገኙዋቸውም ። እርሳቸውም ፡ ወደ ፡ ሴት ፡ አያታቸው ፡ ወደ ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ጐሻም ፡ ተሸግረው ፡ ተደብቀው ፡ ሳለ ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ እናታቸው ፡ እተ ደበቁበት ፡ በታ ፡ ወይናቸው ፡ ያጥቢያ ፡ ከከብ ፡ መስሎ ፡ ተወለዱ ፡ ይባላል ። ወይናቸውም ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የጠራ ፡ ስመሆኑ ፡ አያሌ ፡ ባለቅኔዎች ፡ ተቀኝተውላቸዋል ።

አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ገና ፡ ወቅም ፡ ስያበጁ ፡ የቦረን ፡ ጋሎች ፡ መደ ፡ ጐሻም ፡ ዘምተው ፡ አባታቸውን ፡ ገራም ፡ ፋሲልን ፡ ገድለው ፡ እርሳቸውን ፡ ማርከው ፡

መሰዱዋቸው። ከሁለት ፡ ዓመት፡በኋላ፡ግን ፡ በመተማው ፡ በላባት፡በደጃች ፡ አስበ ፡ ርዳታ ፡ ወደ ፡ጐጃም ፡ ለመመለስ ፡ በቱ ። እንደ ፡ ተመለሱም ፡ በአጼ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ እናት ፡ በንግሥት ፡ አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ ቤት ፡ (የአጼ ፡ ሚናስ ፡ በለቤት ፡) እየተማሩ ፡ አደጉ ፡ ይባላል ። በኋላም ፡ እቴጌይቱ ፡ ለል ጃቸው ፡ ለአጼ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ሰዐቸው ። እርሳቸው ፡ ግን ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፡ እንደ ፡ ተንሣባቸው ፡ ዐውቀው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ ይኖሩ ፡ ጀመር ። አጼ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ልጃቸው ፡ አጼ ፡ ያዕቆብ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስን ፡ በመልክም ፡ ወይን ፡ አይመስክቱዋቸውም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ወቅም ፡ ስላገኙ ፡ ከአጼ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉና ፡ የጦር ፡ ዕድል ፡ አግኝተው ፡ ገደሉዋቸው ። ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ ሐመልማል ፡ ትውልድ ፡ በኋላም ፡ እትዬ ፡ (መንዝ ፡ ሣር ፡ ምድር ፡) በን ፡ አፍሮ ፡ አይገባ ፡ አገር ፡ (ዳሩህ ፡ በሚባል ፡ ቀበሌ ፡) ከዘሸ ፡ ኩሎና ፡ ከወይዘሮ ፡ ድንግል ፡ ሞገሳ ፡ የተወለዱ ፡ የእቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ የወን ድም ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። ከጐጃም ፡ ከባላባት ፡ ወገን ፡ የሚወለዱ ፡ ናቸውም ፡ ይባላል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ወ. ሐመልማል ፡ ከአቤቶ ፡ ፋሲል ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስንና ፡ አቤቶ ፡ ልሳነ ፡ ክርስቶስን ፡ ወልደው ፡ አቤቶ ፡ ፋሲል ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ የማን ፡ ክርስቶስን (ራስ ፡ ጣሀለ ፡ ክርስቶስን ፡ ራስ ፡ አፈ ፡ ክርስቶስን ፡ ራስ ፡ ከናፍረ ፡ ክርስቶስን ፡ ራስ ፡ ብዕለ ፡ ክርስቶስን ፡ ከደጃች ፡ ወልደ ፡ ሐዋ ርያት ፡ ወልደው ፡ ሲኖሩ ፡ በ፲፰፻፯፻፲፭ ፡ ዓ. ም. ሞቱ ።

አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ በይፋት ፡ ያሉትን ፡ እስላሞች ፡ ፈጅተው ፡ ስምንት ፡ አምባዎች ፡ አፍርሰው ፡ ሲመለሱ ፡ መንገዝ ፡ መደምደሚያው ፡ አገር ፡ ለመክ ረም ፡ መረጡ ። በዚህችም ፡ አገር ፡ ከረሙ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ሕግን ፡ ከምት ጠብቅ ፡ ጠበይዋ ፡ ከማረ ፡ በንጽሕናና ፡ በቅድስና ፡ ከምትኖር ፡ ከሥልጣን ፡ ሞገሳ ፡ / የቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ ወልድ ፡ ሠዓላ / ጋራ ፡ ተጋብተው ፡ ወይዘሮ ፡ መለኩዕዊትን ፡ አጼ ፡ ፋሲልን ፡ ራስ ፡ ማርቆስን ፡ አቤቶ ፡ ከናፍረ ፡ ክርስ ቶስን ፡ ራስ ፡ ገላውዲዎስን ፡ ወይዘሮ ፡ ገሊላዊትን ፡ መይዘሮ ፡ መንጌላዊትን ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ሐዋርያትን ፡ ወለዱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከአራድማው ፡ ባላባት ፡ ከደጃዝማች ፡ ፋሪስ ፡ ጋራ ፡ በለጋራ ፡ ነበሩና ፡ ቍርባን ፡ የተበለው ፡ የደጃዝማች ፡ ፋሪስ ፡ ልጅ ፡ እናታቸውን ፡ እትዬ ፡ ሐመልማልንና ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ መንጌ ላዊትን ፡ ወደ ፡ መርሐ ፡ ቤቴ ፡ መስዶ ፡ በቤቱ ፡ አስቀምጠ ፡ በረኃብና ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ ያስጨነቃቸው ፡ ነበር ። ደጃች ፡ ፋሪስም ፡ ከታሰሩበት ፡ ከይፋት ፡ ከዮልዮስ ፡ እጅ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ሣር ፡ ምድር ፡ ሄደው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከይፋት ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ደጃች ፡ ፋሪስን ፡ ይዘው ፡

በግዘት ፡ አስቀመጡዋቸውና ፡ እናታቸውንና ፡ ልጃቸውን ፡ ከቍርበን ፡ ቤት ፡ መስደው ፡ መደ ፡ ጐጃም ፡ ተሻገሩ ፡ ይባልል ። ደጃች ፡ ፋሪስም ፡ በግዘት ፡ በታ ፡ መንዝ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ በሺ፯፻ ፡ ዓ. ም. ሞቱ ።

እላይ ፡ እንደተባለው ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከይፋት ፡ እንደ ፡ ተመለሱና ፡ ደጃዝማች ፡ ፋሪስም ፡ ከዮልዮስ ፡ እጅ ፡ አምልጠው ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስን ፡ ለመውጋት ፡ ከግሸ ፡ ስምንት ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ የያዙ ፡ ወንዶች ፡ አሞጥቶው ፡ ቢቻለኝ ፡ እገድላለሁ ፡ ቢሳንኝ ፡ እሸሻለሁ ፡ ብለው ፡ ፎክረው ፡ ሄደው ፡ ነበርና ፡ እንዳሰቡት ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ ታስረው ፡ በግዘት ፡ እንዳሉ ፡ ለሞት ፡ በቁ ።

ስለ ፡ እንሞር ፡ ጦርነት ።

ሱስንዮስ ፡ እናታቸውንና ፡ ልጃቸውን ፡ መደ ፡ ጐጃም ፡ ከሸኙ ፡ በኋላ ፡ የእንሞርን ፡ አውራጃ ፡ ለመገብኘት ፡ ሲሄዱ ፡ የጉበኙት ፡ ሌላው ፡ አገር ፡ በደንብ ፡ ሲቀበላቸው ፡ የእንሞር ፡ ሕዝብ ፡ ሊመጋቸው ፡ ተንሥቶ ፡ አብረዋቸው ፡ የነበሩት ፡ እስኳልና ፡ ታማኝ ፡ ሎሌዎቻቸው ፡ ራስ ፡ ዮልዮስ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጀግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ ቈይተው ፡ እስኳል ፡ ተመግቶ ፡ ወድቆ ፡ ሰለ ፡ ሱስንዮስና ፡ ዮልዮስ ፡ ደርሰውለት ፡ የወጋውን ፡ የእንሞርን ፡ አዝማች ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው ። እንሞርም ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከብቱንና ፡ ሀብቱን ፡ ይዘውበት ፡ ሄዱ ።

የአጼ ፡ ሱስንዮስና ፡ የአቤቶ ፡ ጸጋ ፡ ክርስቶስ ፡ ጦርነት ።

የአጼ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ አቤቶ ፡ ገላውዲዎስ ፡ ከገራቸው ፡ ሰይመጡ ፡ ሲቀሩ ፡ ወንድማቸው ፡ አቤቶ ፡ ጸጋ ፡ ክርስቶስ ፡ ያባታቸውን ፡ አልጋ ፡ ለመመለስ ፡ ሹሺ ፡ መታደር ፡ ይዘው ፡ ከአጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ በሰንዓር ፡ በኩል ፡ ሸሽተው ፡ ሲሄዱ ፡ ያገሩ ፡ ንጉሥ ፡ አርበት ፡ ያባትህን ፡ አልጋ ፡ ላስመልስልህ ፡ ከፈቀድህ ፡ ልጀን ፡ አግባና ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰጥቼህ ፡ ከሱስንዮስ ፡ ጋራ ፡ እንደገና ፡ ተዋጋ ፡ ቢላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥታትና ፡ መሳፍንት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ አገራቸውን ፡ ለማስወጋት ፡ አለመፍቀድ ፡ ልምዳቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የአርበትን ፡ ምክር ፡ በመቃወም ፡ መደ ፡ ኤሮፓ ፡ ሄደው ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ በ፲፰ሺ፯፻፴ ፡ ዓ. ም በሕመም ፡ ሞተው ፡ ከርዲናል ፡ ሬሺሊዩ ፡ የተባለው ፡ የንግሥት ፡ ልጆች ፡ ይቀበሩበት ፡ በነበረው ፡ ቦታ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ አስቀበሯቸው ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ እቴጌይቱ ፡ በልጃቸው ፡ በአጼ ፡ ያዕቆብ ፡ መሞት ፡ ቢያዝኑም ፡ ዙፋኑ ፡ ከዘራቸው ፡ ስላልወጣ ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስን ፡ የአጼ ፡ ያዕቆብን ፡

ሱሌምች ፡ እንዳያጉላሉና ፡ ከሥልጣናቸው ፡ እንዳይቀንሱባቸው ፡ ቃል ፡ ከገቡዋቸውና ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ልማድ ፡ ከመረቁዋቸው ፡ በኋላ ፡ እርሳቸው ንም ፡ በገዛ ፡ ሀብታቸው ፡ ባሠሩት ፡ በማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲቀብሩዋቸው ፡ ነግረው ፡ ከጥቂቶች ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ዐርፈው ፡ እንደ ፡ ቃላቸው ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ እቴጌይቱን ፡ መላውን ፡ መኳንንትና ፡ አገሬውን ፡ ሰብስበው ፡ በታላቅ ፡ እጀብና ፡ ክብር ፡ በዚያው ፡ በማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀበሩዋቸው ። እቴጌይቱ ፡ ማዕርጋቸው ፡ ሳይቀነስባቸው ፡ በእቴጌነት ፡ ኖረው ፡ በዚያው ፡ ማዕርጋቸው ፡ ተቀበሩ ።

እቴጌይቱ ፡ ይፈሩት ፡ የነበረው ፡ ደርሶ ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከልጃቸው ፡ ከአጼ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ከገደሏቸው ፡ በኋላ ፡ ሚያዝያ ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፮፻፭ ፡ ዓ. ም. ጉጃም ፡ ቀራንዮ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ተብለው ፡ ነገሡ ።

ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ትንቢቶች ፡ ሲነገሩ ፡ ቈይተው ፡ ተፈጽመው ፡ በየ ታሪኩ ፡ መዘግብት ፡ ተቀርጸው ፡ ይኖራሉ ።

ለምሳሌ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ መሰን ፡ ገና ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ልጃቸው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ ከአፍቀሬ ፡ ጐሌ ፡ ልጅ ፡ ከመ ይዘር ፡ ዘነበ ፡ ወርቅ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ስለ ፡ መለዱ ፡ የምሥራች ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ቢልኩ ፡ ስሙን ፡ ምኒልክ ፡ እንድትለው ፡ ብለው ፡ መክረዋቸው ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ የሚገዛ ፡ ምኒልክ ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሣል ፡ እየተባለ ፡ የሚ ነገር ፡ ንግር ፡ ነበርና ፡ ንግሩ ፡ የደረሰ ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ጣይቱ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ታቀናለች ፡ እየተባለ ፡ ይነገር ፡ ነበርና ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ ጣይቱ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ፈልገው ፡ አግብተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ሆኖም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንኳ ፡ ባይሆን ፡ የምኒልክም ፡ የጣይቱም ፡ ንግር ፡ በዓይማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተፈጸመ ፡ እንጂ ፡ አልቀረም ።

ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ መሰን ፡ ልጃቸውን ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ መሰን ፡ ሰገድን ፡ በብረት ፡ ይሞታሉ ፡ የሚል ፡ ንግር ፡ አባታቸው ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ ይጠነቀቁላቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የፈሩት ፡ ይደርሳል ፡ የጠሉት ፡ ይመጣሳል ፡ የተባለው ፡ ምሳሌ ፡ በበኩሉ ፡ ተፈጸሚነት ፡ አግኝቶ ፡ እንደ ፡ ወትሮ ፡ ልማድ ፡ እንደ ፡ አልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ሆኖ ፡ እመ ኝታ ፡ ቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ያድር ፡ የነበረው ፡ አገልጋያቸው ፡ በስለት ፡ መጋ ቸውና ፡ ተናንቀው ፡ እጁን ፡ ጠምዝዘው ፡ ይዘውት ፡ ሲተናነቁ ፡ ሌላው ፡ አገ ልጋያቸው ፡ ደርሶ ፡ የሚተናነቃቸውን ፡ አገልጋይ ፡ በሾተል ፡ ቁራርጦ ፡ ኀሳት ፡

መስጥ፡ ጨመረው ። እርሳቸውም ፡ መዲያውኑ ፡ ነፍሳቸው፡ ከሥጋቸው፡ ተለየች ፡ ይባላል ።

የተለቀሰላቸውም ፡ ልቅሶ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ መሆኑን፡ታሪክ ፡ጸሐፈ ፡ዜና ፡ ድፈጥ ፡ ይገኛል ።

ምን ፡ እበላው ፡ ምን ፡ እለብሰው ፡ ብሎ ፡ ለምን ፡ ይጨነቃል ፡
ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ጉልበት ፡ የሰጠ ፡ እምላክ ፡ ያውቃል ።
ከምድር ፡ ዳር ፡ እምድር ፡ ዳር ፡ ሲገዛ ፡ በድምጡ ፡
ከራውና ፡ ባሪያው ፡ ምንው ፡ አልተቀጡ ።
አያችሁለት ፡ መይ ፡ ይህ ፡ ሙላጅ ፡ ትዕቢቱ ፡
ከቀድሞ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ አብሮ ፡ መተኛቱ ።
ለሌላው ፡ መድኀኒት ፡ ሰጥቶ ፡ የሚያድን ፡
ባሪያ ፡ ጣለው ፡ አሉ ፡ መሰን ፡ ሰገድን ።

የልዩ ፡ ልዩ ፡ ትንቢቶችን ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ተመለከትን ፡ እንግዲህ ፡ መደ ፡ ሥረ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ።

አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ከሞና ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ከተጉለት ፡ ለቀው ፡ መንዝ ፡ አመ ራጃ ፡ ሲደርሱ ፡ ገሚ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በሚባል ፡ ቀበሌ ፡ ጦርነቱን ፡ ለመቀጠል ፡ ሲጄዱ ፡ በተባለው ፡ ቀበሌ ፡ ላይ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለልጃቸው ፡ ለአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ሰጥተው ፡ ምስጢር ፡ ለማውጣት ፡ ከቆውኑ ፡ ለማይጠረጠሩትና ፡ ታሪካቸውንና ፡ የሀገራቸውን ፡ መሰን ፡ ከማናቸውም ፡ መረራ ፡ በመጠበቅና ፡ በመከላከል ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ጀግንነታቸው ፡ ለታወቀው ፡ ለማይደፈሩት ፡ ለመንዝ ፡ ባላገሮች ፡ አደራ ፡ ብለው ፡ ትተዋቸው ፡ ሄዱ ። ይህንንም ፡ ማድረጋቸው ፡ ዘር ፡ እንዳይጠፋ ፡ ታሪክ ፡ እንዳይደፈርስ ፡ በማሰብ ፡ ነው ።

አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደራ ፡ በመንዝ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መመላመል ፡ ጥለው ፡ ሲጄዱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አልተለያቸውም ፡ ነበር ። ሕዝቡም ፡ አደራውን ፡ በመጠበቁ ፡ ከውረጃው ፡ ውጭ ፡ ከሉት ፡ አገሮችና ፡ ሕዝብ ፡ የተለየ ፡ ኀፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ አለው ።

ይኸው ፡ የመንዝ ፡ አውራጃ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የትውልድ ፡ መክታተያ ፡ ዙፋን ፡ ሆኖ ፡ እሁንም ፡ የጥንት ፡ ደረጃውንና ፡ ታሪኩን ፡ አለቀቀም ። አቤቶ ፡ ያዕቆብም ፡ ከበለአደራዎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ጋራ ፡ እንድም ፡ ጊዜ ፡ ቅርታ ፡ ሰይገባቸው ፡ ወንድም ፡ ሴትም ፡ ወልደው ፡ ሲኖሩ ፡ በወንድማቸው ፡ በአጼ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ እዚያው ፡ መንዝ ፡ ባ[illegible] ፡ ዓ ም ፡ ዐረፉና ፡ በአጼ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ከተማ ፡ ታላት ፡ ጎዘን ፡ ሆኖ ፡ ሰንበተ ።

ከዚህ፡በኋላ፡የአቤቶ፡ያዕቆብ፡የታላቁ፡ልጃቸው፡የአቤቶ፡ፋሲል፡ልጅ፡ከእጼ፡ሱስንዮስ፡ጀምሮ፡የኢትዮጵያ፡ነገሥታት፡እየተባሉ፡እስከ፡፲፰፡ነገሥታት፡እስከ፡እጼ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ፡ድረስ፡መናገሻ፡ከተማቸውን፡ጉንደር፡ላይ፡አድርገው፡በሙሉ፡ኢትዮጵያን፡ገዝ ተዋል ።

ይህ፡ሁሉ፡ሲሆን፡የአቤቶ፡ያዕቆብ፡ትንሹ፡ልጃቸው፡አቤቶ፡ሥላሠ፡ቃል፡ከተመለጹበት፡አገር፡ከመንዝ፡አልመጡም (1*) ። ምንጊዜም፡ቢሆን፡አንድ፡ጊዜ፡ያ፡ይንበርያዕቆብ፡ይኖራል፡ተብሏልና፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የተመሰንውና፡የታዘዘው፡ዙር፡በጊዜው፡እስኪደርስ፡ድረስ፡ምስጥናቸውን፡እንደ፡ያዙ፡እስከ፡አቤቶ፡ኃጢኒ፡ክርስቶስ፡ድረስ፡በዝግታ፡እየተራመደ፡የዙፋን፡ርስራ፡መፈንጠቅ፡ጀመረ ።

(1) ባጀጀጀጀ፡ኀ. ም. ልውል፡መርድ፡አዝማች፡አጽፋ፡ወሰን፡ይተመስሉ፡ጸጋ፡ጎመታቸው፡ከወሎ፡ማዚታቸው፡ከደሴ፡ከተማ፡ወደ፡አሊስ፡አበባ፡ስመምጣት፡ጉዞ፡ሲጀምሩ፡አፀደሞቸው፡የንጽሬት፡ስመ፡ጥሩዎች፡ጀግኖችና፡መማክርቶች፡እንደሻዝማች፡ፍትረ፡ማርያም፡እንፈታውራፊ ንጋ፡ስሙ፡እንፈታውራፊ፡ዘውዲ፡ብሩ፡እንፈታውራፊ፡መኩንን፡ብርቤ፡እንፈታውራፊ፡ማህል፡ድንግል፡እንልጅ፡ተፈራ፡ገመልዩ፡እንፈታውራፊ ታምራት፡እንደሻገማች፡ገረሱ፡እንባላምባራስ፡ማንተሙ፡ሥላሴ፡እንክቡር፡ደሻዝማች፡ኃይለ ሥላሴ፡በላይነህ፡እንክቡር፡ደሻዝማች፡መንገሻ፡ወሰኔ፡ሌሎችም፡ሲሞኑ፡እንልጅ፡ተፈራ፡ገመልዩ፡ከመገዛቸው፡በኖት፡ተሸይተዋቸዋል ። ልውል፡አልጋ፡ወራሽም፡መንገሻቸውን፡ሲቀጥሉ፡የንጉሣ፡እትባለው፡በታ፡እንዳ፡ደረሱ፡ሥልጡ፡ሕዝቁ፡ሸኙቷቸው፡ሲመለስ፡ቅን ግርተኛው ፡የመንዝ፡ሕዝብ፡ሲወርድ፡ሲዋረድ፡ከአባቶቹ፡የደረሰለትን፡ታሪክ፡በመገን ዜብ፡ንዘንና ደስታን፡በማቀላጥል፡ተቀብሎ፡እንደ፡ታሪክ፡ልማዱ፡ንፈዶና፡መጥኑን፡ፍረዳውን፡ሳይቀር፡አዘጋጅቶ፡ሞላሌ፡ላይ፡እንዲያድሩለት፡መልካም፡ፈቃዳቸውን፡ለምኖ፡አሳድሮዋቸዋል ። አደጋ፡እኳያደርስባቸውም፡እጅግ፡በመሥጋት፡ጀግናው፡የመንዝ፡ሕዝብ፡መንዱም፡ሌቅም ሲጠብቃቸው፡አድሮ፡በማግስቱ፡ሞፈር፡ውሃን፡አሻግሮ ያባ ቶጅቸው፡ከተማ፡መደምቅሆን፡ሰላ፡ድንጋይ፡ድረስ፡ሸኝቷቸዋል ።

በመሰንባቢያውም፡ጊዜ የመንዝ፡ሽማግሌዎች፡የቀናገሩት፡ትክክለኛ፡ቃል፡ከዘህ፡የሚከተለው፡ነው ።

« ጌታችን ልጃችን፡ሆይ ! ከናትና፡ከባትህ፡በደኅና፡ለመገናኘት፡ያብቃህ ። እኛ ንም፡ቸር፡ወራ፡ለመልማት፡ያቁቃን ። ሲሉ፡ልብ፡በሚነካ፡እንንገር ተሰናብተዋቸው፡ሲመ ለሱ፡የንጉዝብ፡ስጦታ፡ቢያቀርቡላቸው ፤ « ሲሆን፡ቢሾሰን፡ላንተ፡ንበር፡እንጂ፡መስጠት፡አሾማ፡እጉተ፡ደኅና፡ከሆንክ ደህን ፡ስጦታ፡መቼ፡እናጣዋለን ። » ብለው፡ተሳጥሰው፡ተመልሰዋል ። ደህንንና ደህን ፡የመሳለለውንም ፡ኔፍተኛ ፡ያገርና፡የወገን ፡ፍትሮ ፡ብማየት፡ባጀጀጀጀ ፡ኀ. ም. ጠላቅ ፡መንዝን ፡ብመረረ ፡ጊዜ ፡በብጣግሌዎች ፡ በሕፃናትና ፡በመጣ ቸው ፡ላይ ፡የእረመኔነት ፡ተግባሩ ፡እንደ ፡ተፈጸመባቸው ፡አይቀኖል ።

ውስተኛዱቱ ፡የታሪክን ፡ሀብቅ ፡ተጉናጽፋ ፡የምቅኖረው ፡የመርሐ ፡ቤቱ ፡እውራኛ ፡ከዚ ያው ፡ከመንድሮች ፡ጎረቤቶቿ ፡አገር ፡ከመንዝ ፡አቀብልል ፡የጉደለ ፡ላይሆን ፡ሕዝቢ ፡ግር

ማዊ ፡ ንኑ ፡ ንገሥት ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ ፍቢ ፡ ከተማ ፡ ድረስ ፡ ሸኝቶ ፡ እንደ ፡ ተመልስ ፡ አይተኖል ።

እንዲሁም ፡ ፀቅድሞ ፡ ጊዜ ፡ ዮሲትም ፡ በንገሠችበቅ ፡ ዘመን ፡ ፀአንበላ ፡ ሙድም ፡ ላይ ፡ መርንት ፡ አድርጋ ፡ ጠሩን ፡ ሰመቀጠል ፡ ወደም ፡ ለማገድ ፡ ስላልቻል ፡ ወደ ፡ ቃጣኙ ፡ ወደ ፡ መንገዣ መርሐ ፡ ቤቱ ፡ ሕዝብ ፡ መጠጋት ፡ ግድ ፡ ሆንበት ።

ዮሲት ተከታትላ ፡ ብትመጣም ፡ የመንገዣ ፡ የመርሐ ፡ ቤቱ ፡ ጀግኖች ፡ ንጉሣቸውን ፡ ሳያስደፍሩ ፡ መሲረሻ ፡ አሳዮተው ፡ እንዳባረሩዋት ፡ ታሪክ ፡ ይንሳረናል ።

ጠላትም ፡ አገራችንን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ ፅላት ፡ ጊዜ ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ መፀ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ቢመጋ ቸው ፡ በታላት ፡ ጀግንነት ፡ ተክላክለው ፡ አገራቸውን ፡ በሙሉ ፡ እንዲወር ፡ አላስቻሉትም ። በዚ ሁም ፡ ቂም ፡ የቅንጣ ፡ ዝተቅ ፡ የለበለ ፡ ሰው ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ የመንገ ፤ ወይም ፡ የመ ርሐ ፡ ቤቱ ፡ ተወላጅ ፡ ይሆናል ፡ በግለት ፡ በጠላት ፡ ጥይት ፡ ያልተገደለ ፡ የለም ። ማናቸውም ፡ የጠላት ፡ ጥገኛ ፡ የሆን ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ዳኝነት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሆኖ ፡ ንበር ።

እንዚህ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌላቸው ፡ የመንገዣ ፡ የመርሐ ፡ ቤቱ ፡ አሙሓጅዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንገሥት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሆነው ፡ መገሃቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ዘሬያቸው እሳት ፤ መሐላቸው ፡ ንጉስ ፡ ተብለው ፡ ቢጠሩም ፡ ተገቢ ፡ ስማቸውን ፡ አገኙ ፡ ማለት ፡ ነው ።

መንገዣ ፡ መርሐ ፡ ቤቱ ፡ ደህነ ፡ በመሰለ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሲገኙ ፡ ከነርሱ ፡ የሚወለደው ፡ ሁሉ ፡ ምንኛ ፡ ክብር ፡ ይሰማው ፡ ይሆን ። ?

ማናቸውም ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ከተወጠነ ፡ ምክንያት ፡ ይፈጠርለታልና ፡ አቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ተለይተው ፡ በዚሁ ፡ በታሪክዊው ፡ አውራጃ ፡ በመንዝ ፡ ቀርተው ፡ ሰለ ፡ መይዘሮ ፡ ንግሥት ፡ ወዜብ ፡ የተባሉትን ፡ የበጌምድር ፡ የባላባት ፡ ልጅ ፡ አግብተው ፡ ሮ ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወልደው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። — የነርሱም ፡ ስም ፡ ቅጥሎ ፡ የተመለከው ፡ ነው ።

አቤቶ ፡ ፋሲል ፡ (ገራም ፡ ፡)
አቤቶ ፡ ሥግወ ፡ ቃል ፡
አቤቶ ፡ ተገዝረ ፡ ቃልና ፡
መይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ማርያም ፡

እግዚአብሔር ፡ ለመፈጸም ፡ ለሚፈቅደው ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ይፈጥ ርለታል ፡ የተባለበት ፡ የሸዋ ፡ ባላባቶች ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ውጊያ ፡ አጼ ፡ ኢያ ሱን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ እንዲመጡ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ መራቸው ።

አጼ ፡ ኢያሱ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ ጉብኝተው ፡ ባላባቶቹን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በንድ ፡ ከንጋገሩ ፡ በኋላ ፡ ብልጉ ፡ አቤቶ ፡ ንጋሤ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቀርበው ፡ እጅ ፡ የአጼ ፡ ልብን ፡ ድንግል ፡ ዘር ፡ ነኝ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ንገሩዋ

ቸው፡ ዘለግታቸውንና፡ ውበታቸውን፡ ቅልጥፍናቸውንም አተኩረው፡ ተመልክተዋቸው፡ ኖሮ፡ ዝናቸውንና፡ መልክም፡ስማቸውንም፡ይሰሙና፡ ይደንቁ፡ ስለ፡ ንበር፡ እንተማ፡ ወንድሜ፡ ነህ፡ በማለት፡ ንጉሣዊ፡ ሰውነታ ቸው፡ በደስታ፡ ተሞልቶ፡ የበላይነት፡ ምስፍናውን፡ ለንጋሢ፡ ክርስቶስ፡ ሰጥቼዋለሁ፡ እሱን፡ ተከተሉ፡ ብለው፡ ለየባላባቶቹ፡ በዐዋጅ፡ አስታወቀው፡ የጦር፡ መሣሪያና፡ ሽልማት፡ ጨምረው፡ ስለ፡ ሰዉነቸው፡ ባለጋራ፡ ሆነውባቸው፡ ይኖሩ፡ የነበሩትን፡ ሁሉ፡ አስደነገጠ ።

አጼ፡ ኢያሱም፡ እነዚህን፡ ባላባቶች፡ አስማምተው፡ መደ፡ ጐንደር፡ በሚመለሱበት፡ ጊዜ፡ አቤቶ፡ ንጋሢ፡ ክርስቶስን፡ አገር፡ ታያለህ፡ ከዘመ ዶችህም፡ ትተዋወቃለህ፡ ብለው፡ ይዘዋቸው፡ ሄዱ ። የማዕርግ፡ ስምና፡ ማኅተም፡ ይዘው፡ ተመለሱ፡ የሚሉም፡ አሉ ። እንዳንድቹ፡ ደግሞ፡ የሄዱትም፡ በኋላ፡ ነው፡ እንጂ፡ ከንጉሡ፡ ጋራ፡ አብረው፡ አልሄዱም፡ ይላሉ ።

የሆነ፡ ሆኖ፡ ጐንደር፡ ሄደው፡ ንጉሡ፡ በክብር፡ ተቀብለዋቸው፡ ከየዘመዶቻቸውም፡ ከንጋሢዎቹ፡ ልጆች፡ ጋራ፡ ማስተዋወቃቸው፡ እርግጥ፡ ነው ። ጐንደር፡ የተቀመጡት፡ ኟ፡ ዓመት፡ ነው፡ ይባላል፡ ይህን፡ ያህል፡ ዓመት፡ የፈጀባቸው፡ ጐዳይ፡ ምንኛ፡ ከፍተኛ፡ ቢሆን፡ ነው ። እንደሚባለው፡ በአጼ፡ ኢያሱና፡ በልጃቸው፡ በአጼ፡ ተክላ፡ ሃይማኖት፡ መከከል፡ የተነሣው፡ ጠብ፡ እንዳይመለሱ፡ አውኳቸው፡ ነው፡ ይባላል ።

ነገር፡ ግን፡ ሌላ፡ ምክንያት፡ ቢኖረው፡ ነው፡ እንጂ፡ በጠቡ፡ ምክንያት፡ ብቻ፡ አይመስልም ።

ንጋሢ፡ ክርስቶስም፡ የሄዱበትን፡ ጐዳይ፡ አከናውነው፡ መደ፡ አገራቸው፡ ለመመለስ፡ ሲሉ፡ በድንገተኛ፡ በሽታ፡ ታመው፡ ወርፈው፡ ጐንደር፡ ፈት፡ አበ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ እንደ፡ ንገሥታት፡ ልጆች፡ መነ፡ በታላቅ፡ ክብር፡ ተቀበሩ፡ ይባላል ።

እንደ፡ ታመው፡ የተናዘዙት፡ የኑዛዜ፡ ቃል፡ መደ፡ ሸዋ፡ መጥቶ፡ ነበርና፡ በኑዛዜው፡ላይ፡ አልጋዬን፡ ላክዋ፡ ወሬንና፡ የብር፡ ከራዬን፡ ለስብስቴ፡ ንጉዘቤንና፡ ርስቴን፡ ለቀሩት፡ ልጆቼ፡ ለንአቤቶ፡ ዳኛ፡ ለንአቤቶ፡ ሽንቆ፡ ለንአቤቶ፡ ዮናኤልና፡ ለወ/ መርቂት፡ ሰጥቻለሁ፡ የሚል፡ ኑዛዜ፡ስለ፡ተሰማ፡ አቤቶ፡ አክዋን፡ በአጋንቻ፡(መንዝ)፡በባታቸው፡አልጋ፡ስሉ፡ አስቀመጡዋቸው፡ በዘመኑ፡ ዝናም፡ ስላልዘነመና፡ ጊዜው፡ ረኃብ፡ስለ፡ሆነ፡ በንጉሡ፡ በቸት፡ ዓመት፡ ሕዝቡ፡ መክሮ፡ ከልጋቸው፡ አውርዶ፡ መንድማቸውን፡ አቤቶ፡ ዳኛን፡ በልጋው፡ ተክ ። አቤቶ፡ ዳኛም፡ ሯ፡ ዓመት፡ ያህል፡ እንደ፡ቂዩ፡ ከሙርድ፡ አዝማች፡ ሰብስቴ፡ ጋራ፡ ጠብ፡ ተነሣና፡ አልጋውን፡ አስለቅቀው፡ ስፍራቸውን፡ እንደ፡ያዙ፡ ቀሩ ። ከዚያ፡ ወዲህ፡ ማንም፡ ሊደፍራ-

ቸው፡ስላልቻለ፡ተጥቃ፡መሥመሩን፡ሳይለቅ፡የርሳቸው፡ትውልድ፡ዙፋኑን፡እንደ፡ያዘ፡እስከዚህ፡እስካለንበት፡ዘመን፡መንግሥት፡ደረሰ ።

አቤቶ፡ንጋሢ፡ክርስቶስ፡በኑዛዜ፡ያረጋገጡት፡አልጋቸውን፡ላከዋ፡በማለት፡ነበር፡እንደ፡ኑዛዜው፡ሳይሆን፡ቀረና፡አቤቶ፡ዳኛ፡ተተኩ ። ነገር፡ግን፡ከዚህም፡አልፎ፡አልጋው፡በእግዚአብሔር፡ጥበብ፡ለስብስቴ፡ረጋ ።

ስብስቴ፡በየጊዜው፡ያልጋው፡መዛወር፡እየቀጠለ፡መጂዱን፡ባዩ፡ጊዜ፡ከመንድሞቹ፡ጋራ፡ከምጣላና፡እዚሁ፡ደልቶኝ፡ከምኖር፡ለጌታ፡አገልጋይ፡በመሆን፡ተሾማሬ፡መኖር፡ይሻለኛል፡በማለት፡ቁርጠው፡ወደ፡መርሐ፡ቤቱ፡ሄደው፡በዚያን፡ጊዜ፡በመርሐ፡ቤቱ፡እንደ፡ንጉሥ፡ሆኖ፡ይገዛ፡ለነበረው፡መዘምር፡ለተባለ፡መስፍን፡አገልጋይ፡ሆኑ ።

መስፍኑ፡ስብስቴ፡የአቤቶ፡ንጋሢ፡ልጅ፡መሆናቸውን፡ስላወቀ፡ይጣላቸውና፡ክፉ፡ይመኝላቸው፡ስለ፡ጀመረ፡የአጋንንቱም፡ሕዝብ፡እርሳቸውን፡ስለ፡ወደደ፡እናትሀ፡ታመዋልና፡በፍጥነት፡ድረስ፡ብሎ፡ምክንያት፡ፈጥሮ፡ወደ፡አገራቸው፡መለሳቸው ። ስብስቴም፡ወደ፡አገራቸው፡ከተመለሱ፡በኋላ፡በሚናቸውም፡ረገድ፡በመርንትም፡ሆነ፡ባስተዳደሩ፡ንይለኛ፡ስለሆኑ፡መንድማቸው፡ዳኛ፡ከሽከሮቻቸው፡ጋራ፡መከረው፡ቢገጥሚቸው፡ስብስቴ፡ድል፡አድርገው፡ሲመለሱ፡አብቴ፡ጦርና፡ከራውን፡ያወረሰኝ፡አቅንተሀ፡ግዛ፡ለማለት፡ያሰበው፡ትርጓሜ፡ነውና፡ላቡቴ፡ለንጋሢ፡ክርስቶስ፡ሙሉ፡አስለቅሳለሁ፡በማለት፡ሕዝቡን፡ሸላ፡ሚዳ፡ላይ፡ሰብስበው፡ሙሉ፡ሆኖ፡ዋለ ። ይህን፡ጊዜ፡መርድ፡አዝማች፡ያላለ፡ሰው፡ሁሉ፡እንዲቀጣ፡ዐዋጅ፡ንግረው፡መርድ፡አዝማች፡ስብስቴ፡ተሰኙ፡የዚህም፡የማዕረግ፡ስም፡የመጣው፡ከእርሳቸው፡ወዲህ፡ነው ።

በዚያው፡ዕለት፡ለስብስቴ፡ከዚህ፡ቀጥሎ፡ያለው፡ግጥም፡ተደረሰ፡

የንጋሢ፡ልጆች፡አልተስማሙም፡ከቶ፡
አባታቸው፡ቢሞት፡ሰበት፡ልጆች፡ትቶ፡
እንዱን፡እንዱ፡ጠላው፡ሁከት፡አስነሥቶ፡
ስብስቴም፡ለቀቀ፡ሄደ፡ከገር፡ወጥቶ፡
ከወንድሞቹ፡ጋር፡መጋደልን፡ጠልቶ ።

ወደ፡ቆላ፡ወርዶ፡አደረ፡ለጌታ፡
ጌታውም፡ወደደው፡ሰጠው፡ከበሬታ፡
እደን፡ሄደ፡ጌታው፡ሠራዊት፡ሲፈታ፡

ባንድ፡ውርወራ፡አስቀረው፡ጉሹን፡በቱመታ፡
የጉሽ፡ሰንበር፡በላ፡ቁኝ፡እጁም፡በረታ ።

ለጌታው አንድ፡ሰው፡ትንቢት፡ቢነግረው፡
የሱን፡ዘር፡ስብስቱ፡ኋላ፡እንዲገዛው፡
በወደደው፡ፈንታ፡ፈጽሞ፡ጠላው፡
ሊያስረውም፡ፈለገ፡ደግሞም፡ሊገድለው፡
ጋላ፡አስቸግሯቸው፡እጅግ፡ተጨንቀው፡
ዘመዶቹ፡ላኩ፡ምክንያት፡አርገው፡
እናትህ፡ታመዋል፡ድረስ፡ና፡ብለው፡
የቅንነት፡እምላክ፡ከሞት፡አዳነው ።

ሊታሰር፡ተመክሮ፡ሲሉ፡ነገ፡ሠልስት፡
እናትህ፡ታመዋል፡ብለው፡ነገሩት፡
ደንግጠ፡ተነሣ፡በዚህ፡ምክንያት፡
ፈጥኖ፡አገሩ፡ሄደ፡ሳይሰናበት፡
ቢፈልገው፡ቢያጣው፡ልክ፡መደ፡ቤት፡
ያ፡ቆለኛ፡ጌታው፡ሠንበት፡ጸጸት፡
እያለ፡ተከዘ፡ምነው፡በሞትሁት፡
ምነው፡በደለማ፡በፈት፡በያዝሁት፡
አመለጠኝ፡ብሎ፡ነደደ፡እንደ፡እሳት፡
የእግዚአብሔርን፡ፈቃድ፡ያስቀረ፡መስሎት፡
አምላክ፡የፈቀደው፡ያሰበው፡ከጥንት፡
ምን፡ቢሆን፡አይቀርም፡በሴላ፡ብልኀት፡
በክንቱ፡ነው፡እንጂ፡እንዲያው፡መታከት፡
በትእዛዝ፡አይሆንም፡አልጋና፡መንግሥት፡
ከላይ፡ክልፈቀደ፡አምላክ፡ጸበያት ።

ኑጋሚም፡አዘዘ፡አልጋውን፡ላክዋ፡
ዝናም፡አልዘንም፡አለ፡በግዛቱ፡ሸዋ፡
አምላክ፡በይፈቅድለት፡ሰው፡ሁሉ፡ጠላዋ ።

ዳኛም፡ማንባር፡አጣ፡አላገኝም፡ግርማ፡
በስብስቱ፡ጉልበት፡አልጋውን፡ተቀማ፡

ስብስቱ፡ተመርጦ፡አምላክ፡ፈቅዶለት፡
ለልጅ፡ልጁ፡ሆነ፡የሸዋ፡መንግሥት ።

በአልጋ፡ላይ፡የሚቀመጥ፡ማናቸውም፡ንጋጢ፡ተቀዋሚና፡ተቃራኒ፡ስለሚበዛበት፡አቤቶ፡ሽንቁም፡በበክላቸው፡ከወንድማቸው፡ከአብስቱ፡ጋራ፡ግጭት፡እንዲያደርጉ፡መሞከራቸው፡ታውቋል ። እንዲያውም፡አንድ፡መንድ፡ልጅ፡ቢወልዱ፡ስሙን፡ወራሴ፡አሉት ። ስብስቱም፡አልጋ፡በስም፡ይወረስ፡መስሎአቸው፡ያገሩን፡ታላላት፡ሽማግሌዎች፡ሰብስበው፡የልጁ፡ስም፡እንዲለወጥ፡አማላጅነት፡ወደ፡አቤቶ፡ሽንቁ፡ላኩዋቸው ። አቤቶ፡ሽንቁም፡የሚበቃ፡ርስትና፡ንብረት፡ከተቀበሉ፡በኋላ፡ልጃቸውን፡መራሴ፡ፈላሴ፡የሚል፡ስም፡ሰጡት ። መራሴ፡ማለት፡መራሽ፡ማለት፡ሲሆን፡ፈላሴ፡ማለት፡ስደተኛ፡መጻም፡ዘላን፡ማለት፡ነው ።

በስብስቱ፡ንጉሰኛነት፡በዚህ፡ንገር፡ጥርጣሬ፡አድሮባቸው፡በቆሎ፡ባይነቱበት፡ኖሮ፡ያልጋቸው፡መዛወር፡ያሠጋቸው፡ንበር ። ይህም፡የተባለበት፡የመሸም፡ምሾት፡የነባራቸው፡ሁሉ፡መራሴ፡መራሴ፡እያሉ፡በቃለ፡አጋኖ፡አንዱ፡ራእይ፡አየሁ፡ሲላውም፡የራእይ፡ተርጓሚ፡በመሆን፡ሰያጋጩቸው፡አልቀረም ። ንበር ። ይህ፡ያልጋ፡ንገር፡በመሆኑ፡ለታሪክ፡ጸሓፊዎች፡ሁሉ፡ንገር፡ብርቃቸው፡ንውና፡በጉጉለ፡ሞልተው፡በታሪክ፡ላይ፡አስፍረውት፡ሲገኝ ። ለሰጊ፡መይም፡ላንበቢ፡ቅር፡ያሰኛል፡ማለት፡ነው፡እንጂ፡መንድማማች፡የሆን፡ሁሉ፡በየምክንያቱ፡ሳይጣላ፡የሚኖር፡የለም ። ሁለቱ፡መንድማማቾች፡መታረቃቸው፡በጀ፡እንጂ፡በደታረቁ፡ኖሮ፡መቼውንም፡ሁለት፡አይረታምና፡የትኛው፡እንደሚሞት፡አይታወቅም፡ንበር ።

መርድ፡አገማች፡ስብስቱ፡ከልጃቸው፡ጋራ፡በተጣሉ፡ጊዜ፡እጁን፡ይዝ፡አበራለሁ፡የሚል፡ሐሳብ፡ኖሮዋቸው፡እንደ፡ሆነ፡ነው፡እንጂ፡እሞታለሁ፡መይም፡እገድላለሁ፡ብለው፡የተነሡ፡አይመስልም ። በመከከሉ፡ሰሙም፡ላይተርለት፡እጀ፡ዛሩ፡ዘሜ፡በማያገባው፡ገብቶ፡ታረክ፡አበላሸ ። ይህን፡በመሰለ፡ንገር፡መርድ፡አገማች፡አብዩና፡ልጁ፡መርድ፡አገማች፡አምኃየስ፡ብቻ፡ያላንዳች፡ቅያሜና፡መሰናክል፡አልጋውን፡በፍቅር፡እንደ፡ተረከቱ፡አይጠረጠርም ። ከዚህ፡በኋላ፡ተከታትዮ፡ትውልድ፡እግዚአብሔር፡እፈቀደለት፡ድረስ፡ንገሩ፡አልጋውን፡ለልጁ፡ሲለት፡አንዱ፡ከንዱ፡በመላቅ፡አገር፡እያስፋፉ፡አስከ፡አጼ፡ቴዎድሮስ፡መምጣት፡ድረስ፡ያገር፡ማቅናታቸውን፡ሥራ፡አላቋረጡም ። ይህም፡በታሪክ፡ተጽፎ፡ይገኛል ።

ይህ፡ከሆነ፡በኋላ፡ስብስቱ፡አባታቸው፡በቁረቁሩት፡ዐይኔ፡በሚባል፡ከተማ፡ሲኖሩ፡ልጃቸው፡አብዩ፡ዶቃቂት፡ላይ፡ለብቻቸው፡ይኖሩ፡ንበር ።

የሸዋን፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ግራኝ፡መሐመድ፡በሙሉ፡ስላቃጠለው፡አብዩም፡በዶቃቂት፡ላይ፡ታቦት፡ለመትከል፡አስበው፡ከባታቸው፡

ከተማ፡ከያኔ፡የቅዱስ፡ሚክኤልን፡ቃበት፡ሸሸገው፡(ሰውረው፡) ሄዱ ። አባታቸው፡ይህን፡ስለ፡ሰሙ፡ተቈጥተው፡ቢሄዱ፡ልጃቸው፡አብዩ፡የጥ ሙጋና፡የከረዩ፡ጋሎች፡አሽከሮቻቸውን፡አረልፈው፡ቁይተው፡ሊወ ጓቸው፡ተነሡ ።

እዚያው፡እተሰለፉበት፡ሾላ፡ሚዳ፡ላይ፡ሲገናኙ፡ዘሚ፡የተባለው፡ አሽከራቸው፡አባታቸውን፡ስብስቱን፡በዕንጨት፡ጦር፡(ጊጤ፡) ገደላ ቸው ። አብዩም፡ይህን፡አሽከር፡ስለ፡አባታቸው፡ተበቅለው፡ያኔውኑ፡ ገደሉትና፡ሾላ፡ሚዳ፡ዛፍ፡ሥር፡ሲቀበር፡ዛፉ፡የዘሚ፡መቃብር፡እየተ በለ፡የበቅሎ፡ማሰሪያና፡የመንገዲኛ፡መቀጣጠሪያ፡ሆኖ፡ቀረ ። ስብስቱ፡ የተወገት፡ሰገድ፡በተባለ፡ዕንጨት፡ስለ፡ሆነ፡የተወገበት፡በታ፡ሸል፡ (ሹል፡) መንዝ፡ይባላል ።

አብዩ፡አሰልፈው፡ከቲዩዋቸው፡ዘማቾች፡መስዋ፡ዋና፡ዋናዎቹ፡ ከዚህ፡በታች፡የተዘረዘሩት፡ሲሆኑ፡በነርሱ፡ስም፡በቅጣጫቸው፡የሚ ገኙት፡መንደሮች፡ተሠይመው፡እስከሁን፡አሉ ።

ዘሚ፡	ዘሚ፡አምባ፡
ተርቤ፡	ተርቤኖስ፡አምባ፡
ሥንቂ፡	ሥንቅ፡አምባ፡
ጋሸ፡	ጋሸ፡አምባ፡
ጐንዴ፡	ጐንዴ፡አምባ፡
ንቤ፡	ንብ፡አምባ፡
ጉ፞ዠ፞፡	ጉ፞ዠ፞፡አምባ፡
አሕመድ፡	አሕመድ፡አምባ፡
አብደላ፡	አብደላ፡አምባ፡

ልጃቸው፡አብዩ፡ስብስቱን፡ዕያኔ፡ማርያም፡በምትባል፡ቤተ፡ክር ስቲያን፡ቅጥር፡ግቢ፡ውስ ፡በክብር፡አስቀበሩዋቸው ።

ስብስቱ፡፲፩፡ዓመት፡ነግሠው፡ያረፉት፡የካቲት፡፳፯፡ቀን፡፲፱፻፲፪፡ ዓ ም. ነው ። አብዩ፡ፈርተው፡ለቀብሩ፡አልሄዱም ። ከጊዜ፡በኋላ፡ ቤተ፡ክርስቲያኑ፡ቀድሞ፡ከነበረበት፡በታ፡ተዛውሮ፡ከፍ፡መዳለ፡ኩረ ብታ፡ላይ፡ሲታነጽ፡የአቤቶ፡ስብስቱ፡አስክሬን፡ከነበረበት፡በታ፡ሰይ ነሣ፡ብዙ፡ጊዜ፡ሲኖር፡የመንደር፡ክብት፡ከመንጋው፡ተለይቶ፡ሲቀ ርም፡የቤተ፡ክርስቲያኑ፡ፍራሽ፡እንደ፡ከሰላ፡ሆኖ፡ቀርቶ፡ንበርና፡የተ ጠየቀ፡ሰው፡እጥንቱ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡አድራሽ፡ፈልጉ፡በማለት፡ ሩንታ፡ስብስቱ፡መቃብር፡ፈልጉ፡ሲል፡ይህ፡የስም፡ጥሬ፡ሲወርድ፡ ሲዋረድ፡እንጉሥ፡ሣህለ፡ሥላሴ፡ዘመነ፡መንግሥት፡ድረስ፡በመድረሱ፡

ንጉ-ሥ፡ ሣዖል፡ ሥላሴ፡ ወዕሙን፡ በሙ-ሉ፡ ጌብረ፡ ብርሃን፡ ሥላሴ፡ ሲያግ ዙት፡ ያበቱ፡ ወዕም ፡ የክብት ፡ መፈለጊያ ፡ ምሪት ፡ ሆኖ ፡ ለምን ፡ ያቀ ራ-ል ፡ በማለት ፡ ተጸኒቱ ፡ ይባላል ።

በንዳንድ፡ ታሪክም ፡ ዘንድ ፡ ወዕሙን ፡ ልጃቸው፡ አብዬ ፡ ሐር ፡ እም ባ ፡ በሚባል፡ ጌብር ፡ አናራት ፡ ያባላል ። ሆኖም ፡ ታሪክ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ምን ጭ ፡ ከያዘ ፡ ዘወትር ፡ ሲቀጥል ፡ እንደሚኖር ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ መሬትም ፡ ከለ በት ፡ ተዛውሮ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ለመሄድ ፡ ስለማይቻል ፡ ያይኔ ፡ ማርያም ፡ የስ ብስቱ ፡ መቃብርም ፡ በዚሁ ፡ ስም ፡ ለመጠራት ፡ ከጀመረ ፡ መለያ ፡ ስሙ ፡ ይኸው ፡ ሆኖ ፡ መቅረቱ ፡ ነውና ፡ እስከ ፡ አሁንም ፡ የስብስቱ ፡ መቃብር ፡ ተብሎ ፡ ቢጠራ ፡ ለታሪክ ፡ ምን ፡ ወይንት ፡ ልዩነት ፡ ይፈጥርበት ፡ ይሆን ?

አብዬ ፡ በነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ከሸዋና ፡ ከጉንደር ፡ መኳንንት ፡ ብዙ ፡ ተንኰልና ፡ እድማ ፡ ሳይደርስባቸው ፡ አልቀረም ፡ አብዬ ፡ ከያሩት ፡ ወላ ስማ ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተው ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ ጎደላቸው ፡ ስለ ፡ ጠነከረ ፡ በንድም ፡ በኩል ፡ ሚስታቸው ፡ ወ ታጉንስዮያ ፡ የማማ ፡ የሩፋኤል ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እፍሮ ፡ አይገባ ፡ የተባለ ፡ ፈጌዋና ፡ የእ ናታቸው ፡ ወገኖች ፡ ስለረዱዋቸው ፡ ሥጋታቸው ፡ ጠፍቶ ፡ በባታቸው ፡ አልጋ ፡ ተቀመጡ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ መኖሪያቸውን ፡ ከዶቃቂት ፡ ወደ ፡ ሐር እምባ ፡ ከተማ ፡ አዘውረው ፡ የቅዱስ ፡ ሚክኤልን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠር ተው ፡ አባታቸው ፡ ከቀኑት ፡ ከዐዋጂ ፡ መንዝ ፡ አልፈው ፡ እስከ ፡ እደራራ ፡ መንዝ ፡ አለሙት ። ባለቤታቸው ፡ መ ታጉንስዮያ ፡ ሲሞቱ ፡ ቀድሞ ፡ ከባታ ቸው ፡ ሳያስፈቅዱ ፡ መስደው ፡ በደበሩት ፡ በዶቃቂት ፡ ቅዱስ ፡ ሚክኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀብረው ፡ መቃብራ ቸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ተከብሮ ፡ ይኖራል ። ያገሩም ፡ ፈጌዋና ፡ ሽማግሌ ፡ ከሃናቱም ፡ ሳዶምር ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ ይሰጡ ታል ። በየጊዜው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የሚደረው ፡ አገልግሎት ፡ ለመቃብ ራቸውም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ መጠን ፡ ይደረግለታል ። በደንቡም ፡ የሚ ጠበቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከሀገ ፡ ለማጠን ፡ በሚገባበት ፡ ጊዜ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ እንጂ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንብቶ ፡ ለማየት ፡ በፍጹም ፡ ክልክል ፡ ነው ። አብዬ ፡ በነገሡ ፡ በሸሪ ፡ ዓመት ፡ በየክቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፩፰፻፯፻፲፯ ፡ ዓ. ም. ወርፈው ፡ አልጋቸውን ፡ ልጃቸው ፡ አምኃየስ ፡ ያዙ ።

ሙ. አገማች ፡ አምኃየስ ፡ ከወደዘር ፡ ዕዑብና ፡ መርድ ፡ አገማች ፡ አስፋ ፡ መሰንን ፡ አይክልን ፡ የመርቅ ፡ ውሃን ፡ ወልደው ፡ ሲኖሩ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የላ ስታንና ፡ የጉንደርንም ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘር ፡ ተክሩይ ፡ ለመሆን ፡ የወደዘር ፡ ትውንን ፡ ልጅ ፡ ወደዘር ፡ አትሞች ፡ ሆኖን ፡ እንደ ፡ ቁጥት ፡ አድርገው ፡ የፈተኛዋ ፡ ባለቤታቸው ፡ እያሉ ፡ አስቀመጡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከመ

ይዘሮ፡ አትሞች ፡ ሆኖ ፡ ልጅ ፡ ሳያገኙ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲኖሩ ፡ ልጃቸው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ከትምህርት ፡ ቤታቸው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ቤት ፡ ሲመለሱ ፡ ወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖ ፡ በሚኖሩበት ፡ አገር ፡ በኩል ፡ ሲያልፉ ፡ እዚያው ፡ አገር ፡ መሸቶባቸው ፡ እወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖ ፡ ቤት ፡ በእንግድነት ፡ ሲያድሩ ፡ ያባታቸው ፡ ቁባት ፡ መሆናቸውን ፡ ባለማወቅና ፡ ሴቲቱም ፡ የበላቸው ፡ ልጅ ፡ መሆናቸውን ፡ ባለማወቅ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ተገናኝተው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ተፀነሡ ። መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሲያድጉ ፡ በናታቸው ፡ በወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖ ፡ በኩል ፡ የላስታና ፡ የጉንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘር ፡ መሆናቸውን ፡ ሲያውቁ ፡ አባታው ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አትበሉ ፡ ራስ ፡ በሉኝ ፡ ሲሉ ፡ ቁይተው ፡ እንደ ፡ ነና ፡ ንጉሥ ፡ በሉኝ ፡ ማለት ፡ ጀመሩ ፤ የሚገባቸው ፡ ሆኖም ፡ በመገኘቱ ፡ ንጉሥም ፡ ራስም ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ ነበር ።

የነወይዘሮ ፡ ትውን ፡ ከጉንደር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መግባት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ወይዘሮ ፡ ትውን ፡ ያኽስታቸውን ፡ ልጅ ፡ አስኳልን ፡ ወንድማቸውን ፡ ወልከኛ - ኡልያስን ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖን ፡ ይዘው ፡ አፈት ፡ ራሰቸውን ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሲመጡ ፡ ግሼ ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ፡ ከንጉሡ ፡ ከአምኃየስ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙተው ፡ ንጉሡ ፡ ለወይዘሮ ፡ ትውን ፡ የቀመትን ፡ ግዛት ፡ ለመልከኛ ፡ ኡልያስ ፡ የጥቅሚን ፡ ግዛት ፡ ለአስኳል ፡ የደብደበን ፡ ግዛት ፡ ለአትሞች ፡ ሆኖ ፡ የሰላ ፡ ድንጋይን ፡ ግዛት ፡ ሰጥተው ፡ አንረዋቸው ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የአምኃየስ ፡ ልጅ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ የወለዱት ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ቤት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲመለሱ ፡ ወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖን ፡ እግዛታቸው ፡ ሰላ ፡ ድንጋይ ፡ ስለ ፡ አገኙዋቸው ፡ ነው ።

አስፋ ፡ ወሰን ፡ ከባታቸው ፡ ቁባት ፡ ከወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ መውለዳቸውን ፡ አባታቸው ፡ መስማታቸውንና ፡ ያባታቸው ፡ ቁባት ፡ መሆናቸውን ፡ ከተገነዘቡ ፡ በኋላ ፡ አባታቸውን ፡ ፈርተው ፡ ሸሹ ።

አባታቸውም ፡ ያለ ፡ ማወቅ ፡ መሆኑን ፡ ከተረዱት ፡ በኋላ ፡ አባታቸው ፡ ይቅርታ ፡ እድርገውላቸው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ሲኖሩ ፡ ኢዮአስን ፡ ከነአፍሮ ፡ አይገባና ፡ ከነጃልዩ ፡ ወገን ፡ ወለዱ ። ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ ወሰን ፡ ሰገድና ፡ ኢዮአስ ፡ ሲያድጉ ፡ ምቀኛ ፡ ገብዮ ፡ ሁለቱን ፡ ወንድማማቾች ፡ በዘር ፡ በማፎካከር ፡ አጣልተዋቸው ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሸፍተው ፡ ሲጌዱ ፡ አባታቸው ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ደርሰው ፡ ይዘዋቸው ፡ እጃቸውን ፡ በሻሽ ፡ አስረው ፡ አመጡዋቸው ፡ ይባላል ። በሻሽም ፡ ያሰሩዋቸው ፡ በብረት ፡ ይሞ

ታሉ ፡ የሚል ፡ ንግር ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ በብረት ፡ ቢያስሩዋቸው ፡ ይሞቱባቸው ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ቦት ፡ ቀን ፡ በሻሽ ፡ አስረው ፡ አቴያተው ፡ ፈቱዋቸው ፡ ይባላል ።

የሸሹበትንም ፡ ምክንያት ፡ ቢጠይቁዋቸው ፡ ምስጢራን ፡ ከገለጸላቸው ፡ በኋላ ፡ የባላባትነት ፡ ቀደምትነት ፡ ለእርሳቸው ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑንና ፡ ከታናሽ ፡ ወንድማቸው ፡ ከኢዮአስ ፡ ብልጫ ፡ እንደሚኖራቸው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተውላቸው ፡ እባታቸውን ፡ ቤታማኝነት ፡ በማገልገል ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ አቅንተዋል ፡ ይባላል ።

እምኑየስ ፡ ከወይዘሮ ፡ ዕፀብና ፡ የወለዱዋቸው ፡ ቦት ፡ ልጆች ፡ እያሉ ፡ እንዲ ፡ ገና ፡ የመንግሥትን ፡ ዘር ፡ በመፈለግ ፡ ወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖን ፡ ሲያገቡ ፡ ከልጃቸው ፡ የተወለደው ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ ከእርሳቸው ፡ ቢወለድ ፡ ኖሮ ፡ አልጋቸውን ፡ የሚወርስ ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ በመረጡና ፡ ለማንስ ፡ ባደጉ ፡ ነበር ፡ ?

እምኑየስ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ ስለ ፡ በዛላቸው ፡ ሐር ፡ አምባን ፡ እንደ ፡ አልፍኝ ፡ አንኮበርን ፡ እንደ ፡ አዳራሽ ፡ አድርገው ፡ ፴፮ ፡ ዓመት ፡ ከንገሡ ፡ በኋላ ፡ በጥር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ሸኔኒኒኔ ፡ ዓ. ም. ወረፉና ፡ እርሳቸው ፡ ባሠሩት ፡ በአንኮበር ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበሩ ።

እምኑየስ ፡ ሲሞቱ ፡ ልጃቸው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ መሰን ፡ በዙፋናቸው ፡ ተተኩ ። በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ያንኮበርን ፡ ከተማ ፡ እያስፋፉና ፡ እያደረጁ ፡ ሲኖሩ ፡ ዕድሜዎ ፡ አጭር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ መነኮሴ ፡ በማስመሰል ፡ ቢንግራቸው ፡ የመነኮሴውን ፡ ቃል ፡ ከአውነት ፡ በመቁጠር ፡ ረኽቦ ፡ ዕድሜ ፡ በምጽዋት ፡ መስጠት ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑና ፡ ለያድባራቱ ፡ በመስጠት ፡ ግምጃ ፡ ቤቱ ፡ በዎዉን ፡ ሲቀር ፡ ሎሌዎቻቸውም ፡ ቢመክሩዋቸው ፡ ዕድሜዬ ፡ ከረዘመ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እመልሰዋለሁ ፡ በማለት ፡ ተደልለው ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ያፈሩትን ፡ ሀብት ፡ አባክኑት ።

ልጃቸውን ፡ መሰን ፡ ሰገድን ፡ የጦር ፡ አበጋዝ ፡ በማድረግ ፡ በልጃቸው ፡ ጉልበት ፡ ግድምና ፡ ይፍራቻን ፡ አንጽኪያንና ፡ ግሼን ፡ ቀጥሎም ፡ ከጣርማ ፡ በርና ፡ ከቁንዲ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጨበ ፡ ድረስ ፡ ሲገዙ ፡ በሰላሌም ፡ እስከ ፡ ወባይ ፡ ጥግ ፡ ድረስ ፡ እስከ ፡ ጨበና ፡ ጉራጌ ፡ ግዛታቸውን ፡ አስፋፉ ። ሽዋንም ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ከጠፋው ፡ ጀምሮ ፡ የአማራ ፡ ባላባቶች ፡ ተከፋፍለው ፡ ሲገዙት ፡ ቈይተው ፡ አስፋ ፡ መሰን ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ ጠቅልለው ፡ ለመግዛት ፡ ይመኙስለ ፡ ነበረ ፡ መደ ፡ ቆላ ፡ እየወረዱ ፡ በየጊዜው ፡ ስለሚዘምቱ ፡ ጥዱ ፡ የተባለው ፡ የሞረት ፡ ባላባት ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ዘለፋ ፡ በግጥም ፡ ላከባቸው ።

ስፋ ፡ መሰን ፡ ይፋት ፡ ጠንክረው ፡ ይረሱ ፡
ሞረት ፡ ጥዱ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ከመመላለሱ ።

አስፋ ፡ መሰንም ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ።

ለሞፈር ፡ ለቀምበር ፡ ለመቃን ፡ ለገበን ፡ የሚሆነኝን ፡
ሳልቁርጠው ፡ አልተርም ፡ ዘንድሮ ፡ ጥዱን ።

ጥዱ ፡ ሲመልስ ።

ያበቱ ፡ አገር ፡ ሞረት ፡ ሴቱን ፡ ያሳምራል ፡
ወንዱን ፡ ያደረጃል ፡
ምንፍቁን ፡ ያመነጫል ፡
ጠበሉን ፡ ያፈልቃል ፡
ቢለመልም ፡ እንጂ ፡ ጥዱ ፡ መች ፡ ይደርቃል ።

አስፋ ፡ መሰን ።

በጉም ፡ ገበያ ፡ ወጥቼ ፡
ፈረሴን ፡ አጣ ፡ አብልቼ ፡
ሳልቁረጠው ፡ አልቀርም ፡ ዘድንድሮ ፡ ጥዱን ፡
እጅግ ፡ ደብር ፡ ሳይሆን ።

አስፋ ፡ መሰን ፡ እንዳሉት ፡ ሆኖላቸው ፡ በየጊዜው ፡ እየዘመቱ ፡ በላብ ቱን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ በማድረግ ፡ ወደ ፡ ቆላ ፡ ወርደው ፡ የታሰሩትን ፡ እየፈቱ ፡ አገሩን ፡ ለመግዛት ፡ በቁ ።

ለመግዛት ፡ የቻሉበትም ፡ በጦርነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሞረትን ፡ ባላ ባት ፡ ጥዱን ፡ በመደለል ፡ ጦርነት ፡ ቢደረግ ፡ የሕዝቤና ፡ የሕዝብህ ፡ ደም ፡ በከንቱ ፡ ከሚፈስ ፡ እንዲሁ ፡ እያለንበት ፡ እንርጋ ፡ በማለት ፡ ለሞረት ፡ ሕዝብ ፡ ልብስም ፡ እንዲያለብሰ ፡ ገንዘብም ፡ እንዲሰጡ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናቱም ፡ እንዲመጸውቱ ፡ ፈቃድ ፡ ጠይቀውት ፡ ጥዱም ፡ ፈቅዶላቸው ፡ የነገሥታ ትን ፡ ዋና ፡ መሣሪያ ፡ ስብከትን ፡ ይዘው ፡ ሕዝቡን ፡ ያለ ፡ እንዳች ፡ ጦርነትና ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ገዙት ። ጥዱም ፡ ባላባትነቱ ፡ ሳይነካበት ፡ ለንጉሡ ፡ ይገ ብር ፡ ጀመረ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ግዛታቸው ፡ ሰፊ ፡ ሀብ ፡ ቢኖራ ፡ አሽከሮቻ ቸው ፡ ማርዩና ፡ ንግዴ ፡ በየጊዜው ፡ ሕዝቡን ፡ እያሳደሙ ፡ ይሸጡት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በመፈራረሻው ፡ ወደ ፡ ጋላው ፡ አገር ፡ ከድተው ፡ ገቡ ። አስፋ ፡ መሰንም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አዘኑ ፡ ጠላቶቻቸውንእንዲያርቅላቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡

እየለመኑ፡ያትርሱኝ፡ምጽዋታቸውን ፡ለያድባራቱ፡እየሰጡ፡ለክህናት፡ ግብር፡ያበሉ፡ንበር ። ከዕለታትም ፡አንድ፡ቀን ፡ግብር፡በሚያበሉበት፡ ጊዜ፡አንድ፡ቢልተኛ፡ከህን፡ተንሥዶ ፡ሲያሳርግ፡

ንግደ ፡ዳር ፡ዳሩን ፡ያነጽንጽ ፡

አስፋ ፡መሰን ፡ከመንበሩ ፡አይናወጽ ፡

አትርሱኝ፡እየተባልን፡እንድንመጻውኢ፡ብሎ፡መረቀ፡ይባላል ።

መርድ፡አዝማች፡አስፋ ፡መሰን ፡መነኮሲው ፡ሰድሚያቸው፡አጭር፡ ነው ፡ያላቸው ፡መፈጸሙ ፡ቀርቶ ፡ንጉሠነቸውና ፡ሠብታቸው ፡ሲያልቅ፡ እንደ ፡ገና ፡አገር ፡በማቅናትና ፡ማዘታቸውን ፡በማስፋፋት ፡በዕድሚያ ቸው ፡ሠርተው ፡መልሰው ፡ሸዋን ፡ዕረፍ ፡ዓመት ፡ገዝተው ፡በሐምሌ ፡ሯ፫ ፡ቀን ፡፲፰፻፸ ዓ. ም. ዐርፈው ፡አርሳቸው ፡ባሠሩት ፡በቅድስት ፡ማርያም ፡ ቤተ ፡ክርስቲያን ፡አንኰበር ፡ላይ ፡ተቀበሩ ።

አስፋ ፡መሰን ፡በብልኀንት ፡ማዘታቸውን ፡እያስፋፉ ፡ሲኖሩና ፡ይህን፡ ያህል ፡ጊዜ ፡ሲገዙ ፡ስብስቲም ፡ልጃቸው ፡አብዩ ፡የቅዱስ ፡ሚክኤልን፡ ታቦት ፡አሰፈልጓቸው ፡በመስዓም ፡ጠር ፡ከማዘጋጀቱና ፡ልጃቸውን ፡ለመ ሙጋት ፡ከመነሣት ፡ይልቅ ፡እንድነአስፋ ፡መሰን ፡ብልኀንትን ፡በመጨመር ፡ ታቦቱ ፡በዘጌ ፡እንዲመለስ ፡ቢያደርጉ ፡ያበትና ፡ልጅ ፡ታሪክ ፡በንገሥ ታት ፡ታሪክ ፡ሙስጥ ፡በእንደዚህ ፡ያለ ፡አካኼን ፡ተጽፎ ፡መኖሩ ፡ቅር የሚያሰኝ ፡ነው ።

አስፋ ፡መሰን ፡ሲሞቱ ፡ልጃቸው ፡መሰን ፡ሰገድ ፡ተተኩ ፡ አባታ ቸው ፡በሕይወታቸው ፡ሳሉ ፡የመንዝ ፡ባላባት ፡የአፍቀሬ ፡ጐሌ ፡ልጅ ፡ መይዘር ፡ዘነበ ፡መርጥ ፡ባላቸውን ፡ሰው ፡ንድሎባቸው ፡የጎዘን ፡ልብስ ፡ እንደ ፡ለበሱ ፡ለአቤቱታ ፡ሲመጡ ፡የመሰን ፡ሰገድ ፡አገልጋዮች ፡አይተዋ ቸው ፡ኖሮ ፡ለመሰን ፡ሰገድ ፡የሴቲቱን ፡መብትና ፡መልክ ፡ዘርዝረው ፡ቢን ግሩዋቸው ፡ሴቲቱን ፡አግብተው ፡ከዚሁ ፡ጋብቻ ፡ሣህለ ፡ሥላሴ ፡ስለ ፡ተወ ለዱ ፡ልጅ ፡ስለ ፡መውለዳቸው ፡የምሥራች ፡መጀ ፡አባታቸው ፡ቢልኩ ፡ አትዮጵያን ፡እንድ ፡አድርጎ ፡የሚገዛ ፡ምኒልክ ፡የሚባል ፡ይነግሣል ፡እየ ተባለ ፡በዚያን ፡ጊዜ ፡ይነገር ፡ስለ ፡ንበር ፡አስፋ ፡መሰንም ፡ጊዜው ፡የደ ረሰ ፡መስዓቸው ፡ልጁን ፡ምኒልክ ፡በለው ፡ብለው ፡ላኩባቸው ። ነገር ፡ግን ፡የተወሰዱት ፡ሕፃን ፡ምኒልክ ፡መባላቸው ፡ቀርቶ ፡ሣህለ ፡ሥላሴ ፡ ተባሉ ።

ጣይቱ ፡የምትባል ፡ሴት ፡አጎዮጵያን ፡ታቀናለች ፡የሚል ፡ይህን ፡ የመሰለ ፡ንግርም ፡ስለ ፡ንበር ፡መሰን ፡ሰገድ ፡እንደ ፡ገና ፡ጣይቱ ፡የምት ባል ፡ሴት ፡ፈልገው ፡አገቡ ። ነገር ፡ግን ፡ጊዜው ፡ይዘገያል ፡እንጂ ፡የተ

ነገረው ፡ አይቀርምና ፡ ይህ ፡ ንግር ፡ በቮኛው ፡ ትውልድ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒ ልክ ፡ ዘመን ፡ ተፈጸመ ።

ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፡ ጌስ ፡ ላይ ፡ ለአባታቸው ፡ እንደራሴ ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ አባታቸው ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ መኖሪያቸውን ፡ አንከበር ፡ ቁንዲ ፡ ላይ ፡ አደረጉ ። በዘመናቸው ፡ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ የተባለው ፡ እንደራሴ ፡ በጐንደር ፡ ይገዛ ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡን ፡ በዐዋጅ ፡ ሰብስበው ፡ ራስ ፡ በሉኝ ፤ ቀጥሎም ፡ ንጉሥ ፡ በሉኝ ፡ ይህን ፡ ያላለ ፡ ይቀጣል ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ከነገሩ ፡ በኋላ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በተነገረው ፡ ንግርት ፡ መሠረት ፡ ፱ ፡ ዓመት ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ በአገልጋያቸው ፡ እጅ ፡ በስለት ፡ ተወግተው ፡ በሰኔ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ሺ፰፻፺፯ ፡ ዓ ም ፡ ዐርፈው ፡ እርሳቸው ፡ ባሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ በቀኑዲ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተቀበሩ ።

በዕለተ ፡ ዕረፍታቸው ፡ የተለቀሰላቸውም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በትንቢት ፡ መግለጫ ፡ ላይ ፡ እግብተነው ፡ የነበረው ፤ እዚህም ፡ በታው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ አሁንም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ደግመን ፡ እግብተነዋል ።

ምን ፡ እበላው ፡ ምን ፡ እለብሰው ፡ ብሎ ፡ ለምን ፡ ይጨነቃል ፤
ለዚህ፡ ዓለም ፡ ጉልበት ፡ የሰጠ ፡ አምላክ ፡ ያውቃል ።
ከምድር ፡ ዳር ፡ እምድር ፡ ዳር ፡ ሲገዛ ፡ በድምጡ ፤
ከራውና ፡ ባሪያው ፡ ምነው ፡ አልተቀጡ ።
አያችሁለት ፡ ወይ ፡ ይህ ፡ ውላጅ ፡ ትዕቢቱ ፤
ከቀድሞ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ አብሮ ፡ መተኛቱ ።
ለሌላው ፡ መድኀኒት ፡ ሰጥቶ ፡ የሚያድን ፤
ባሪያ ፡ ጣለው ፡ አሉ ፡ መሰን ፡ ሰገድን ።

የንጉሥ ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ ልጆች ፡ አቤቶ ፡ በሱራና ፡ አቤቶ ፡ ዣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ናቸው ። ንጉሥ ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ ሳይሞቱ ፡ ልጃቸው ፡ አቤቶ ፡ በሱራ ፡ የመ ርሐ ፡ ቤቱ ፡ እንደራሴነት ፡ ተሰጥቶዋቸው ፡ ይገዙ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ታላቁ ፡ ልጅ ፡ በመሆናቸው ፡ ንጉሥ ፡ መሰን ፡ ሰገድ ፡ እንደ ፡ ወረቱ ፡ በአልጋው ፡ እንዲ ተኩ ፡ ተጠርተው ፡ ሲመጡ ፡ ደንባ ፡ ላይ ፡ የጅሩ ፡ ጋላዎች ፡ ጠብቀው ፡ ኟ ፡ ቀን ፡ ከተዋጉዋቸው ፡ በኋላ ፡ እዚያው ፡ ገደሉዋቸው ። ሌላ ፡ ወራሽ ፡ ስላል ነበረና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመበት ፤ ታናሹ ፡ ወንድማቸው ፡ አቤቶ ፡ ዣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ይማሩበት ፡ ከነበረው ፡ ከቱሮ ፡ ገዲል ፡ ሥላሴ ፡ ደብር ፡ ተጠርተው ፡ በአጀብ ፡ መጥተው ፤ በተወለዱ ፡ በ፲፰ ፡ ዓመታቸው ፡ በአባታ ቸው ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጡ ። በባታቸውም ፡ ዙፋን ፡ እንደተቀመጡ ፤ ሕዝባቸ ውን ፡ በገንዘብና ፡ በክብት ፡ ስጦታ ፡ እያስደሰቱ ፡ የተቸገረውንም ፡ ድኻ ፡ ግብር ፡ ከመክፈል ፡ እየማሩ ፡ ተወደውና ፡ ተመስግነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

ንጉሥ፡ሣህለ፡ሥላሴ፡ባለታሞው፡አልጋ፡ከተተመጡ፡ጀምሮ፡ፊስም፡ንጉሥም፡ይባሉ፡ስለ፡ንበር፡በመልእክቶችና፡ለማስታወሻ፡በሚሰጡዋቸው፡ዕቃዎች፡ፊስ፡ሣህለ፡ሥላሴ፡ንጉሠ፡ሸዋ፡እያሉ፡ያትሙበዋውና፡ይቀርጹበቸው፡ንበር ።

በጋብቻም፡ረገድ፡በማዛታቸው፡ውስጥ፡ከሚገኙት፡ከባላባት፡ልጆች፡በመጋባትና፡ይህን፡የመሳሰለ፡ዘዴ፡በመሥራት፡ኀይሉና፡ክሕዝቡም፡ስምምነት፡አግኝተው፡የመሠረቱትን፡ከተማ፡አንከበርን፡ዋና፡ከተማቸው፡አድርገው፡ዛፊ፡ሸዋ፡ተብሎ፡የሚጠራውን፡አገር፡በሞላ፡አቀኑ ።



ንጉሥ፡ሣህለ፡ሥላሴ ።

በዚያም፡ጊዜ፡ዛፊ፡አዲስ፡አበባ፡ተብሎ፡የሚጠራው፡የኢትዮጵያ፡ዋና፡መናገሻ፡ከተማ፡በንጉሥ፡ሣህለ፡ሥላሴ፡ተቈርቍሮ፡በጋላ፡ፈንፈኔ፡ይባል፡ንበር ። ዛፊ፡ታላቁ፡ቤተ፡መንግሥት፡በለበትም፡በታላይ፡ድንኳን፡ተክለው፡ግብር፡አብልተው፡ይህ፡በታ፡የልጅ፡ልጅቼ፡ቤተ፡መንግሥት፡ይሠናል፡ሲሉ፡በተናገሩት፡መሠረት፡ይኸው፡እስከ፡ዘመናችን፡ደርሶ፡እናየዋለን ።

ባሁኑ፡ጊዜ፡የመሠረት፡ድንጋይ፡እንደሚጣለው፡እርሳቸውም፡ድንኳን፡ተክለው፡የቤተ፡መንግሥቱን፡ሕንጻ፡መሥሪያ፡በታ፡አመለከቱ፡እግዚአብሔርም፡በዙፋን፡ላይ፡መርጦ፡ሲያከብሟቸው፡ለመጀ

ፈቱ፡ የሚሆነውን ፡ የሚያውቁ ፡ ለመሆናቸው ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አስረጅ ፡ ይሆናል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ንግድና ፡ አገር ፡ ስለሚስፋፋበት ፡ ጉዳይ ፡ ውል ፡ እየተዋዋሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥልጣኔ ፡ ክብር ፡ አሳይተዋል ።

ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ የሸዋ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተብለው ፡ እንዲቀቡ ፡ ቢፈቅዱም ፡ በጊዜው ፡ ጳጳስ ፡ ስላልተገኘ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሳይፈጸምላቸው ፡ ቀርቶ ፡ ንጉሥ ፡ ተብለው ፡ ሲጠሩ ፡ ኖረው ፡ በነገሡ ፡ በ፴፱ ፡ ዓመታቸው ፡ በጥቅምት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ወርፈው ፡ እርሳቸው ፡ በሠሩት ፡ በእንክበር ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበሩ ። በዕለተ ፡ ሰረፍታቸው ፡ ጊዜ ፡ ባለቅኔ ፡ ከዚህ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ቅኔ ፡ ተቀኝላቸው ፡

ደብረ ፡ ሚካኤል ፡ ብክዩ ፡ በላዕለ ፡ እንብዕኪ ፡ ደመ ፡
ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ተስፋኪ ፡ እስመ ፡ ተፈጸመ ።
ውኃለቀ ፡ ለገዚፉ ፡ ወኢይትመየጥ ፡ ዳግመ ።
ወልበ ፡ ግፉዓን ፡ አስተሐመመ ፡
ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ልሳኑ ፡ እምጣን ፡ በሞት ፡ ተሐትመ ።
ወእምተናግሮ ፡ አፉሁ ፡ አርመመ ።
ከመ ፡ ሕልመ ፡ ሌሊት ፡ ሞትከ ፡ ይመስለኒ ፡ ንጉሠ ፡ መግበ ፡ ዓለመ ፡
ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልብከ ፡ ሀላዊ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳመ ፡
በደዌ ፡ ጎይልከ ፡ እምድጎረ ፡ ደክመ ፡
እንዘ ፡ ትብልኒ ፡ አሐውር ፡ እምጌሡም ፡ ጌሠመ ፡
ከመ ፡ ወውሎ ፡ ሞትከ ፡ ቀደመ ።

ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ እንደ ፡ ገለጸው ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ እገባለሁ ፡ እያሉ ፡ ያስቡ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልብከ ፡ ሀላዊ ፡ ደብረ ሊባኖስ ፡ ገዳመ ፡ በደዌ ፡ ጎይልከ ፡ እምድጎረ ፡ ድክመ ፡ ሲል ፡ ገልጾታል ። ገዳም ፡ ሊገቡ ፡ ያሳቸው ፡ አሳብ ፡ በሞት ፡ ስለ ፡ ተቋረጠ ፡ አልተፈጸመም ። ሆኖም ፡ በየጊዜው ፡ ይህን ፡ ተረድተው ፡ ሲያስቡ ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ እንደነአጼ ፡ ከሌብ ፡ እንደነጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደነ ፡ አጼ ፡ ኢያሱ ፡ እድያም ፡ ሰገድ ፡ የዓለምን ፡ ከንቱነት ፡ ተረድተው ፡ ገዳም ፡ ለመግባት ፡ ማሰባቸው ፡ የሚያስመሰግናቸው ፡ ነው ።

ልጆቻቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ በዛብሽ ፡ የተወለዱ ፡ አቤቶ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ወይዘሮ ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡ ወይዘሮ ፡ በለጥሽቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ይመኑሽል ፡ የተወለዱ ፡ ወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፤ መርድ ፡ አዝማች ፡ ኃይሉ ፤ ወይዘሮ ፡ ጠንቁየለሽ ፡ ከሌሎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የባላባት ፡ ልጆች ፡ የተወለዱ።ራስ ፡ ዳርጌ ፤ ወይዘሮ ፡ብርቅነሽ ፤ ወይዘሮ ፡ እያሁሉም ፤ ወይዘሮ ፡

ሙላት፡ መርቅ፡ ሲሆኑ፡ በኋላ፡ ከሚስታቸው፡ ከወይዘሮ፡ በዛብሽ፡ የተወለዱት፡ አቤቶ፡ ኃይለ፡ መለኮት፡ ከእርሳቸው፡ ሞት፡ በኋላ፡ በባታቸው፡ አልጋ፡ ተተኩ ።

አቤቶ፡ ኃይለ፡ መለኮት፡ የሞትንም፡ እኛ፡ ያለንም፡ እኛ፡ ብለው፡ ወሞጅ፡ ተናግረው፡ የሸዋ፡ ንጉሥ፡ ተባሉ ። አጼ፡ በሉኝም፡ ብለው፡ አጼ፡ ኃይሉ፡ ይባሉ፡ ነበር ። ወዲያውም፡ ያባታቸውን፡ አስክሬን፡ ከደብረ፡ ብርሃን፡ ወደ፡ አንኮበር፡ በመለኮትና፡ በንጋሬት፡ እጀብ፡ ወስደው፡ በቅዱስ፡ ሚክኤል፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ቀበሩዋቸው ።

ንጉሥ፡ ኃይለ፡ መለኮት፡ ሰውነታቸው፡ ግዙፍ፡ ነበር፡ ነገር፡ ግን፡ ልበ፡ ቅንና፡ ልበ፡ ሙሉ፡ ስለ፡ ነበሩ፡ አባቶቻቸው፡ እንደሚያደርጉት፡ ወንድ ሞቻቸውን፡ በእስር፡ ቤት፡ እንዲያቁዩዋቸው፡ ቢመክሩ፡ ፈቃዳቸው፡ ባለመሆኑ፡ በነጻ፡ በማኖር፡ በልበ፡ ሙሉነት፡ እየገዙ፡ ኖሩ፡ እንደርሳቸው፡ ያህል፡ በልበ፡ ሙሉነት፡ የገዛ፡ የለም፡ ይባላል ።

ንጉሥ፡ ኃይለ፡ መለኮት፡ ሸዋን፡ ሲገዙ፡ ወሎን፡ የሚገዙ፡ ወይዘሮ፡ ወርቂት፡ ነበሩ፡ በዚህም፡ ጊዜ፡ ጐንደርን፡ በእንደራሴነት፡ የሚገዙ፡ ራስ፡ ዓሊ፡ ስለ፡ነበሩ፡ አጼ፡ ቴዎድሮስ፡ በጎይላ፡ ተንሥተው፡ ራስ፡ ዓሊን፡ መግተው፡ አባረሩዋቸው ። ራስ፡ ዓሊም፡ ሸሽተው፡ ወደ፡ ደራ፡ መጡ፡ እዚያም፡ እንደ፡ ደረሱ፡ አባላባቱ፡ ዋቄ፡ ዲበ፡ ዘንድ፡ ተጠጉ፡ እርሱ፡ ግን፡ አስሮ፡ ለአጼ፡ ቴዎድሮስ፡ አሳልፎ፡ ሊሰጣቸው፡ ሲል፡ ኃይለ፡ መለኮት፡ ከሸዋ፡ ተንሥተው፡ ከዋቄ፡ ዲበ፡ ጋራ፡ ተዋግተው፡ ድል፡ አድርገው፡ ነጻ፡ አውጥተው፡ ወደ፡ ሸዋ፡ አመጡዋቸው ።

ራስ፡ ዓሊ፡ ወደ፡ ተወለዱበት፡ አገር፡ ወደ፡ የጁ፡ እንዲሄዱ፡ ቢጠይቋቸው፡ ከብዙ፡ ሥንቅና፡ ሠራዊት፡ ጋራ፡ ወደ፡ አገራቸው፡ ሸኙዋቸው ። ራስ፡ ዓሊም፡ መዓልትና፡ ሌሊት፡ እንደሚፈራረቁ፡ ደስታና፡ መከራም፡ ጉን፡ ለጉን፡ ስለሚሄዱ፡ ታመው፡ ብዙ፡ መከራ፡ አይተው፡ ባገራቸው፡ በየጁ፡ ዐረፉ ።

አጼ፡ ቴዎድሮስ፡ ወይዘሮ፡ ወርቂትን፡ ለመውጋት፡ ወደ፡ ወሎ፡ ገብተው፡ እርሳቸውን፡ በከረምቱ፡ ወራት፡ ድል፡ አድርገዋቸው፡ ክረምቱን፡ በወሎ፡ አሳልፈው፡ በጥቢው፡ እንደ፡ ገና፡ ሸዋን፡ ለመውጋት፡ መጡ ። በደብረ፡ ብርሃን፡ አታክልት፡ በሚባል፡ ቦታ፡ ከኃይለ፡ መለኮት፡ ጋራ፡ ተዋግተው፡ ድል፡ የማን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሳይታወቅ፡ መሸፉ፡ ንጉሥ፡ ኃይለ፡ መለኮት፡ ቀድሞውንም፡ ታመው፡ ስለ፡ ነበረ፡ የዚያኑ፡ ሌሊት፡ ጥቅምት፡ ፴፡ ቀን፡ ፲፰፻፶፮፡ ዓ. ም. ወርፈው፡ ደብረ፡ በግዕ፡ ገዳም፡ በክብር፡ ተቀበሩ ። ዘመነ፡ መንግሥታቸውም፡ ፳፡ ዓመት፡ ነው ። በማግሥቱ፡ ቁንዲ፡ ላይ፡ ሆነው፡ አጼ፡ ቴዎድሮስ፡ በመንጽር፡ ሲመለከቱ፡ ጋላውና፡ አማራው፡

ሲዋጋ፡አይተው፡የሚዋጋው፡ማን፡ነው፡ብለው፡የኃይለ፡መለኮትን፡እማች፡አቶ፡በድሉን፡ቢጠይቋቸው፡ጋላና፡እማራ፡ነው፡ብለው፡መለሱላቸው። አጼ፡ቴምድሮስም፡ንጉሥ፡የሌለው፡ሕዝብ፡በጀግንነት፡እንዲህ፡ፈጽከኖ፡አይዋጋም፡በማለት፡ጥሬጣሬ፡ገብቶዋቸው፡የኃይለ፡መለኮትን፡መቃብር፡አስከፍተው፡አይተው፡እመኑ። ኃይለ፡መለኮት፡ይህን፡የመሰለ፡ጀግና፡መቃደር፡እያለው፡በይሞት፡ኖሮ፡ይሞክረን፡ነበር፡አሉ፡ይባላል። አቶ፡በድሉና፡የኃይለ፡መለኮት፡አያት፡ወይዘሮ፡ዘነበ፡ወርቅ፡ምንም፡አጼ፡ቴምድሮስን፡እየመሩና፡እየረዱ፡ቢመጡ፡ለዚሁ፡ዋጋ፡አጼ፡ቴምድሮስ፡ምንም፡ያደረጉላቸው፡ውለታ፡እንዳለ፡የሚገልጽ፡ጽሑፍ፡የለም። ምክንያቱም፡አጼ፡ቴምድሮስ፡ጥቅማቸውንና፡ያሰቡትን፡ዓላማ፡ያግኙ፡እንጂ፡በኔም፡ጊዜ፡እንዲሁ፡ነው፡በማለት፡እንዲህ፡ለመሰለ፡ከዳተኛ፡ሰው፡ዋጋ፡ከለመስጠታቸው፡በላይ፡እይመዱትም፡ነበር፡ይባላል። አቶ፡በድሉና፡ወይዘሮ፡ዘነበ፡ወርቅ፡የተቀየሙበት፡ነገር፡እንደሚባለው፡ይህ፡ከዚህ፡ቀጥሎ፡የተጻፈው፡ነው።

አቶ፡በድሉ፡የአቤቶ፡ኃይለ፡መለኮት፡እኅት፡የወይዘሮ፡ወሰን የለሽ፡በለቤት፡ስለ፡ነበሩ፡ያባታቸውን፡ሀብትና፡ርስት፡እንዲያከፍሏቸው፡ቢጠይቋቸው፡ኃይለ፡መለኮት፡ስለ፡ከለከሏቸው፡ነው፡እየተባለ፡በሚነገረው፡ነው።

አጼ፡ምኒልክም፡በአጼ፡ቴምድሮስ፡እጅ፡ተይዘው፡ወደ፡ጐንደር፡ሄዱ። በረከት፡ላይ፡ከተደረገው፡ክፍ፡ያለ፡መርዝት፡በኋላ፡አጼ፡ምኒልክ፡በአጼ፡ቴምድሮስ፡እጅ፡ሆነው፡እየተማሩ፡ዐሥር፡ዓመት፡በጐንደርና፡በመቅደላ፡ከቁዩ፡በኋላ፡አምልጠው፡፲፰፻፶፯፡ዓ.ም. ሰኔ፡፳፬ ቀን፡ወደ፡አገራቸው፡ወደ፡ሸዋ፡ተመለሱ። አጼ፡ቴምድሮስ፡የምኒልክን፡ማምለጥ፡በሰሙ፡ጊዜ፡ልጃቸውን፡ወይዘሮ፡አልጣሽን፡ድረውላቸው፡ስለ፡ነበረ፡አሽከራቱንሳ፡ይሄት፡ሄደ፡ብለው፡ጠየቁና፡አልወሰዷቸውም፡ብለው፡ስለ፡ነገሩዋቸው፡ይዟት፡ቢሄድሳ፡ምን፡ችግሮት፡ኖሩዋል፡አሉ፡ይባላል።

አጼ፡ቴምድሮስ፡በሸዋ፡እንደራሴ፡አድርገው፡ያስቀመጧቸው፡አቶ፡በዛብህ፡ስለ፡ነበሩ፡አጼ፡ምኒልክን፡አሳልፎ፡የሰጣቸው፡አሽከር፡አጼ፡ቴምድሮስን፡ስለ፡ውለታው፡ሹመት፡እንዲሰጡት፡ቢለምኗቸው፡ምኒልክን፡ያህል፡ጌታ፡አሳልፈህ፡ከሰጠህ፡ለኔም፡ጊዜ፡ይኸው፡ነውና፡እንዳች፡ነገር፡አላደርግልህም፡በዛብህን፡ጠይቅ፡ብለው፡አሰናበቱት፡ይባላል።

አቶ፡በዛብህ፡እንደራሴነቱን፡ከመሾማቸው፡በፊት፡አጼ፡ቴምድሮስ፡አቤቶ፡ምኒልክን፡ይዘው፡ወደ፡ጐንደር፡ሲሄዱ፡የንጉሥ፡ሣህለ፡ሥላሴን፡ልኖውን፡ልጅ፡መርድ፡አገማች፡ኃይሌን፡ነበር፡የሾሙት፡

መርድ ፡ አዝማች ፡ ኃይሌ ፡ ፫ት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ በሥልጣን ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፡ ሊሸፍቱ ፡ ማሰባቸውን ፡ አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ እርሳቸውን ፡ ሸረሙ ፡ አሰሯቸው ፡ በእርሳቸው ፡ ፈንታ ፡ የንግሥታት ፡ ዘር ፡ የሌላቸውን ፡ አቶ ፡ በዛብህን ፡ ሾሙና ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ጉንደር ፡ ሊሄዱ ፡ ሲሉ ፡ አቶ ፡ በዛብህን ፡ ጠርተው ፡ እኔን ፡ የክዳውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አመልክተኝ ፡ ብለው ፡ አዘዟቸው ። አጼ ፡ ቴዎድሮስም ፡ አቶ ፡ በዛብህ ፡ ያስታመቋቸውን ፡ ብዙዎችን ፡ የንጉሥ ፡ ኃይሉ ፡ መለኩትን ፡ አሽከሮች ፡ እጅና ፡ እግራቸውን ፡ በመቁረጥ ፡ አካላቸውን ፡ በማጉደል ፡ ቀጡዋቸው ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ አልታሸ ፡

አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ምነው ፡ ተዋረዱ ፡
የሸዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ንሥተውት ፡ ሄዱ ፡

ብላ ፡ አለቀሰች ፡ ይባላል ።

መይዘር አቀማሽ ፡ የአጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልጅ ፡ የአቤቶ ፡ ምኒልክ ፡ ባለቤት ፡ ናቸው።ይህም ፡ ጋብቻ ፡ የተደረገበት ንጉሡ ፡ አቤቶ ፡ ምኒልክ ፡ ከአጼ ፡ ልብን ፡ ድንግል ፡ የመረዱ ሙሆኑ ቸውም ፡ ስለሚያውቁና ፡ ምኒልክ ፡ የንጉንት ፡ ዕድል ፡ እንደሚኖራቸው ፡ ስለሚያውቁ ፡ ከዚህ ፡ ጋብቻ ፡ ዘር ፡ ለማትረፍ ፡ ምኞት ፡ እንደነበራቸው ፡ ታውቋል ።

አቶ ፡ በዛብህንም ፡ ሾመው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ሊሄዱ ፡ ሲነሡ ፡ አቶ ፡ አበዩንና ፡ መኳንንቱን ፡ ጠርተው ፡ የመሰነባበቻ ፡ ግብር ፡ ተደርጎ ፡ ሳለ ፡ እዝማሪ ፡

ጃንሆይን ፡ ባል ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ አምኖ ፡ ይቁርባል ፡
ሲሰኛውን ፡ ጉበዝ ፡ ያራቱን ፡ ማዕዝን ፡ ባል ፡

ሲል ፡ በመልካም ፡ ድምፅ ፡ ሲያዘምር ፡ ትርንሚውንና ፡ ፍቺውን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጣምራ ፡ ጠራቸውንና ፡ ጉራዲያቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ እፈረስ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ፎክሩ ፡ ይባላል ።

አቤቶ ፡ ምኒልክ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ፱ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ቢሄዱና ፡ እዚያው ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቢቈዩ ፡ የእርሳቸው ፡ ያሥር ፡ ዓመት ፡ መለየት ፡ ጊዜ ፡ የሸዋን ፡ ነገሥታት ፡ የግዝ ፡ ንት ፡ መሥመራን ፡ ያቋረጠው ፡ ቢመስል ፡ ያባታቸው ፡ መንግሥት ፡ ለባ ዕድ ፡ እንዳያልፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከአጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እጅ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ሲገቡ ፡ አቶ ፡ በዛብህ ፡ እመንገድ ፡ ቁይተው ፡ ጋዲሎ ፡ ላይ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፶፯ ፡ ዓ ም ፡ ቢዋጉዋቸውም ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ባባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ለመቀመጥ ፡ በቁ ። ያቶ ፡ በዛብህን ፡ የጦር ፡ ጉዞ ፡ የተመለከተች ፡ ሴት ፡ የሚከተለውን ፡ እንጉርጉሮ ፡ ገጠመች ፡ ይባላል ።

ማነው፡ብላችሁ፡ነው፡ጋሽው፡መመልመሉ ፤
ማነው፡ብላችሁ፡ነው፡ጦራችሁ፡መሰሉ ፤
የጌታችሁ፡ልጅ፡ነው፡እረ፡በስመ፡አብ፡በሉ ።

እንዲህ፡ስትል፡ሲሰማ፡መረኛው፡በሙሉ፡ተበተን፡ይባላል ።

ወደ፡ጉንደርም፡ሲሄዱ፡የተባለው፡ይህ፡ነው ።

ቍርጡን፡ወመቁና፡አለመኖርህን ፤
በረከት፡አገቡት፡ጌታዩ፡ልጅህን ።

አቶ፡በዛብህ፡ድል፡ሲሆን፡የተደረሰው ።

አባ፡ድክር፡በዙ፡የበረከት፡ለታ፡አሸንጉ፡ተወግቶ ፤
ከሻንቅላ፡ጋራ፡አብሮ፡ተቈራኝቶ ፤
አልጋ፡ለምኒልክ፡እያለ፡ቈይቶ ፤
ሊመጋቸው፡ሄደ፡የሰው፡ንገር፡ሰምቶ ።

እንተም፡አደረግኸኝ፡የመነሡሴ፡ፈራጅ ፤
የሙት፡ልጅ፡ሲቀበል፡እንዲህ፡ነወይ፡ወዳጅ ።

አቶ፡በዛብህ፡ለሞት፡ፍርድ፡እንደ፡ቀረቡ፡የተፈረደው ።

አቶ፡አባሙርጂ፡የተባሉት፡ጀግና፡በተራቸው፡ለፍርድ፡ተንሥተው፡ሰሉ፡ተልባ፡መጠጥና፡ሰሙ፡በሴ፡የተባሉት፡ያቶ ። በዛብህ ። ጦሮች፡ያጼ ። ቴምድሮስና፡የንጉሥ፡ኃይለ ። መለኮት፡የጦር፡ሠራዊት ። ተጋጥመው፡በደረጉት፡ውጊያ፡የፈጸሙትን፡አገልግሎት፡በደም፡ፍላት፡ጀብዱዎቸውን፡ሲደረድሩና፡አጼ ። ምኒልክም ። ያይን ። ምስክር፡ስለ፡ነበሩና፡እንደ፡አቶ፡በዛብህ፡ጥፋት ። መጠን ። የመጸጸት ። መልክ ። በፈታቸው፡ሳይ፡ተሥሎ ። ይታይ ። ነበር ። እንጂ ። ስለ፡ሕይወታቸው፡ፍጻሜ ። አልተደሰቱበትም ። ነበር ። ይባላል ። አቶ ። አባሙርጂም ። አባ ። ድክር ። በዙ ። ጓደ ። ምን ። ላድርግህ ። ፈረ ። ወግቶሃልና ። እትድንም ። በሚል ። ፍርድ ። ፈርደው ። እያለቀሱ ። ተቀመጡ ። ይባላል ።

አቶ ። በዛብህ ። ተይዘው ። ለፍርድ ። ሲቀርቡና ። በጥፋታቸው ። ፍርድ ። ተሰጥቶ ። ፍርዱ ። ከተፈጸመ ። በኋላ ። የተገጠመው ፤

ጋላም ። አርፈህ ። ተኛ ። አውልቀህ ። ጀርባህን ፤
ያማራውም ። ጉበጣ ። ፍታ ። ኮርቻህን ፤
በሳት ። አቃጠሉት ። የሚያበጃንህን ።

እንተም ። ጨክኝ ። ነበርክ ። ጨክኝ ። አዘዘብህ ፤
እንደ ። ገና ። ዳዩ ። እሳት ። ነደደብህ ።

ስለ፡አቶ፡በዛብህ፡ሞት፡እንዲት ፡አልቃሽ ፡በየጊዜው ፡ሰው፡በሞተ፡ቁጥር፡በየልቅሶው፡ቤትና፡በየማርገፃው፡የልቅሶ፡እንጉርጉሮ፡በመደርደር፡ያበላትን፡ያጠጣትንና፡ያለበሳትን፡በማሞገስ፡እያለቀሰች፡መኖር፡ሥራዋ፡ስለ፡ሆነ፡ከዕለታት፡አንድ፡ቀን፡በሙሾ፡ዜማ፡የንብርን፡መንጋጋ፡ፍየል፡ገብቶ፡ላሰው፡እንዲህ፡አይደለም፡ወይ፡ጊዜ፡የጣለው፡ሰው፡ብላ፡ስለ፡ተናገረች ፡ንጉሡ ፡ምኒልክን፡እንደ፡ፈሪ፡አቶ ፡በዛብህን፡እንደ ፡ጉበዝ፡አድርጋ፡ተናግራለችና ፡ሞት፡ይገባታል፡ብለው፡ከሰሸች ፡ወደ ፡ፍርድ ፡ሸንጎ ፡አቅርበዋት ፡ስለ ፡ነበረና ፡ይኸው ፡መንጀኋ ፡በደበባይ ፡ስለ ፡ተነገረ ፡ችሎት ፡ከነበሩት ፡መኳንንቶች ፡እንደኛው ፡አቶ ፡አበዩ ፡የተባሉት ፡በክሳሹ ፡ላይ ፡ከፍ ፡ያለ ፡መቀሳ ፡ከተናገሩ ፡በኋላ ፡ፈርተን ፡ገድለን ፡አሁን ፡ይህችን ፡ድኻ ፡ሴት ፡ላንዳንድ ፡እፍኝ ፡ንፍሮ ፡ስትል ፡ለፍልፋ ፡በኖረች ፡ትሙት ፡ትባላለች ፡ስትሞት ፡አይታየኝም ፡ብለው ፡ተናግረው ፡ከፈሩሱ ፡በኋላ ፡ድሮውንም ፡ያቶ ፡በዛብህ ፡መሞት፡ጸጸቱ ፡ከልባቸው ፡አልጠፋ ፡ኖሮ ፡ንጉሡ ፡ፍርዳቸው ፡ቅን ፡ነበርና ፡የአቶ ፡አበዩን ፡ንግግርና ፡ፍርድ ፡በመገንዘብ ፡ሴትዮዋን ፡በነጻ ፡ከማሰናበታቸው ፡በላይ ፡እንደ ፡ልቧ ፡ትናገር ፡ብለው ፡የገንዘብም ፡ርዳታ ፡ስለ፡ፈቀዱላት ፡ያች ፡ድኻ፡ሴት ፡አልልታዋን ፡እያቀለጠች ፡ሄደች ፡ይባላል ።

ይህ ፡ሁሉ ፡ሲሆን ፡እጴ ፡ምኒልክ ፡ባባቶቻቸው ፡አልጋ ፡እንደ ፡ገና ፡ለመቀመጥ ፡አብቅታቸው ፡ንጉሠ ፡ሸዋ ፡ተብለው ፡ሥስት ፡ዓመት ፡እንደ ፡ንጉሥ ፡እጴ ፡ቴምድሮስ ፡በየጊዜው ፡ከዳተኛ ፡እየተነሣባቸውና ፡የእንግሊዝም ፡ጦር ፡ስላመከቸው ፡እጴ ፡ምኒልክን ፡ለመክታተልና ፡ወደ ፡ሸዋ ፡ለመምጣት ፡ጊዜው ፡ሳይፈቅድላቸው ፡ቀርቶ ፡በነገሡ ፡በ፲፩ ፡ዓመታቸው ፡በ፲፰፻፷ ፡ዓ. ም. መቅደላ ፡ላይ ፡ሞቱ ።

እጴ ፡ቴምድሮስ ፡ሲሞቱ ፡የተገጠመላቸው ።

መቅደላ ፡አፋፉ ፡ላይ ፡ፈዩኽት ፡በረከተ ፡
የሴቱን ፡እናውቅም ፡ወንድ ፡እንድ ፡ሰው ፡ሞተ ።

እንበሳው ፡መቅደላ ፡ወድቆ ፡አገኘሁት ፡
ሰው ፡እያየው ፡መሸሽ ፡ነውር ፡ሆኖበት ።

መቅደላ ፡አፋፉ ፡ላይ ፡ቢኖሣ ፡ሁክታ ፡
ገበሬም ፡ወደ ፡ቤት ፡ተልባም ፡ወደ ፡ጐታ ።

እናትና ፡አባቱ ፡አላንድ ፡አልወለዱ ፡
አባ ፡ታጠቅ ፡ሞተ ፡ያ ፡ወንዱ ፡ያ ፡ወንዱ ።

ማረክን ፡ እንዳይሉ ፡ ሰው ፡ የለ ፡ በጃቸው ፡
ገደልን ፡ እንዳይሉ ፡ ሞተው ፡ አገኙዋቸው ፡
ምን ፡ አሉ ፡ እንግሊዞች ፡ ሲገቡ ፡ አገራቸው ፡
ለወሬ ፡ አይመቹ ፡ ተንኩለኛ ፡ ናቸው ።

የአጼ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ አስተያየት ፡ ወስነውታል ።

አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሽፄ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በገዙበት ፡ ጊዜ ፡ ባደሩት ፡ ዓመታት ፡ ፲፰፻፴፰—፲፰፻፵፭ ፡ ዓ. ም. ውስጥ ፡ ሕዝባቸውን ፡ እንደ ፡ ንጉሥና ፡ እንደ ፡ አባት ፡ አስተዳደሩት ። በሽቱ ፡ ዓመታት ፡ ፲፰፻፵፭ ፡ አስከ ፡ ፲፰፻፵፮ ፡ ዓ. ም ውስጥ ፡ ሕዝባቸውን ፡ በሰይፍ ፡ ጨፈጨፉት ። በመጨረሻዎቹ ፡ አራት ፡ ዓመታትም ፡ ፲፰፻፵፮—፲፰፻፷ ፡ ዓ. ም. ውስጥ ፡ ሕዝባቸውን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉት ፡ ይላሉ ።

በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ግን ፡ ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ነገሡ ፡ ሲባል ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ የሽፍትነታቸውንም ፡ ጊዜ ፡ ጭምር ፡ ከዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ጋራ ፡ ቁጥረዉት ፡ ይሆናል ።

አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በፋሲካ ፡ ማግሥት ፡ የማዕዶት ፡ ዕለት ፡ ሚያዝያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፷ ፡ ዓ. ም. መቅደላ ፡ ላይ ፡ ሲሞቱ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ አዝማቾች ፡ የመንግሥት ፡ ልብሳቸውንና ፡ ዘውዳቸውን ፡ ልጃቸውንም ፡ ልዑል ፡ ዓለማየሁን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ይዘው ፡ ሲወስዱ ፡ ልዑል ፡ ዓለማየሁ ፡ እንደ ፡ ግዳይ ፡ ምልክትና ፡ እንደ ፡ ድል ፡ መንሸ ፡ ማስረጃ ፡ ሆነው ፡ ቢሄዱም ፡ እዚያው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ ቁይተው ፡ ታመው ፡ ሞቱና ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀበሩ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ገና ፡ አልጋ ፡ መራሽ ፡ ሳሉ ፡ አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በሞቱ ፡ በሃኛው ፡ ዓመት ፡ በ፲፱፻፲፭ ፡ ዓ. ም. የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ሊጐበኙ ፡ ሄደው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ያጼ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዘውድና ፡ ልብስ ፡ መንግሥት ፡ ይዘው ፡ ተመለሱ ።

አጼ ፡ ምኒልክም ፡ የክፍተኛውን ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ዘውድና ፡ ዙፋን ፡ ወርሰው ፡ የመጣባቸውን ፡ ጠላት ፡ በታማኞች ፡ ወንድሞቻቸውና ፡ ሎሌዎቻቸው ፡ ክንድ ፡ ርዳታ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ በንጉሥነት ፡ ሽፀ ፡ ዓመት ፡ ከፎ ፡ ወር ። በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ሽፀ ፡ ዓመት ፡ ከፎ ፡ ወር ፡ በድምሩ ፡ ሳኟ ፡ ዓመት ፡ ከሄ ፡ ወር ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ገዝተው ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ እንድም ፡ ቀን ፡ ሳያፍሩ ፡ ቁይተው ፡ በ፲፱፻፭ ፡ ዓ. ም. ወረፉ።

ከመሞታቸውም ፡ አስቀድሞ ፡ አልጋ ፡ መራሽ ፡ ይሁ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ከየመኳንንቱ ፡ ጋራ ፡ አስተዋውቀዋቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤



ዳግማዊ እጼ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ከርሰቸው ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ አያሱ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ገዝተው ፡ ቢ፲፱፻፱ ፡ ዓ. ም. አልጋውን ፡ ስለ ፡ ለቀቁ ፡ በዚሁ ፡ ዓ. ም. የአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ልጅ ፡ ዘውዲቱ ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ ተብለው ፡ ነገሡ ።

ይህ ፡ ዘርፍ ፡ የመጣው ፡ ያቤቶ ፡ ያዕቦብን ፡ ቅጥቶኛ ፡ መሥመር ፡ ይዘ ፡ ከአቤቶ ፡ ሥግው ፡ ቃል ፡ የቀጠለ ፡ ሲሆን ፡ የወንድሞቹ ፡ የነአጼ ፡ ፕላ



ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፤

ሙዲምስ፡ የነአጼ ፡ ሚናስና ፡ የነአቤቶ ፡ ፈቅጦርን ፡ ፍጻሜ ፡ በጥቂቱ ፡ ማስረዳት ፡ ያሻልና ፡ መደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ ይሀን ፡ መሥመር ፡ በጭራ ፡ እናጥና ።

ገ ፡ ይነግሥ ፡ የተባለው ፡ ገላውዲዮስ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ገዝተው ፡ ሞቱ ።
ፈ ፡ ይመውት ፡ የተባለው ፡ ፈቅጦር ፡ በግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ።

ሚ ፡ ይሡይጥ ፡ የተባለው ፡ ሚናስ ፡ በጦርነቱ ፡ ሙስጥ ፡ ተማርከው ፡ መደ ፡ የመን ፡ አገር ፡ ምርኮኛ ፡ ሆነው ፡ ሄደው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁም ፡ የግራኝ ፡ ልጅ ፡ ከታላላቅ ፡ የጦር ፡ አዝማቾች ፡ ጋራ ፡ በጼ ፡ ገላውዲዮስ ፡ እጅ ፡ ተማርከው ፡ ነበረና ፡ የምርኮ ፡ መመላለስ ፡ ሆኖ ፡ የግራኝም ፡ ልጅ ፡ ከነዓደ ጮቹ ፡ መደ ፡ አገሩ ፡ ሚናስም ፡ ከነዘመዶቻቸው ፡ መደ ፡ አገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገብተው ፡ ከአጼ ፡ ገላውዲዮስ ፡ በኋላ ፡ አፄ ገሙን ፡ ወርሰው ፡ ፱ ፡ ዓመት ፡ ነግሠው ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ ልጃቸው ፡ አጼ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ፴፯ ፡ ዓመት ፡ ነግሠው ፡ መንግሥቱ ፡ ከልጅ ፡ ልጅ ፡ እየተወራረሰ ፡ እስከ ፡ አጼ ፡ ያዕቆብ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ይነበር ፡ የተባለው ፡ ትንቢት ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ከአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ከገራም ፡ ፋሲል ፡ የሚወለዱት ፡ አጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ነግሠው ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘርፍ ፡ ተያይዞ ፡ እስከ ሁኑ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘርፍ ፡ ድረስ ፡ እየቀጠለ ፡ መጣ ።

አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በ፲፭፻ ፡ ዓ. ም. ነግሠው ፡ በ፲፭፻፴፫ ፡ ዓ. ም. ዐረፉ ። በለቤታቸውም ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ መንጌል ፡ እስከ ፡ ልጃቸው ፡ እስከ ፡ አጼ ፡ ሚናስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ሁሉ ፡ በም ክርና ፡ በማበረታታት ፡ እየረዱ ፡ ቈይተው ፡ ዐረፉ ።

ወይዘሮ ፡ መሉተ ፡ ማርያም ፡ ያቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ፡ እርሳቸውም ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ክፍሌን ፡ አግብተው ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ክርስቶስን ፡ ወይዘሮ ፡ ሮማን ፡ ወርቅንና ፡ ወይዘሮ ፡ ጎልቀት ፡ ድንግልን ፡ መሉዱ ። ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ክርስቶስ ፡ ፮ ፡ ልጆች ፡ ወይዘሮ ፡ ሮማን ፡ ወርቅ ፡ ፮ ፡ ልጆች ፡ ወልደጦል ፡ እነዚህ ፡ ፲፪ቱ ፡ የክምክም ፡ ዙፋን ፡ ወይዛዝሮች ፡ ሲባሉ ፡ ይኖራሉ ።

በጐጃም ፡ እጅግ ፡ በዝተው ፡ የሚገኙት ፡ ባላባቶች ፡ ሁሉ ፡ የወይዘሮ ፡ መሉተ ፡ ማርያም ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። ስለ ፡ አቤቶ ፡ ተገክረ ፡ ቃል ፡ የዘር ፡ መክታተል ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ የተገለጸ ፡ ነገር ፡ አልተገኘም ፡ ምክንያቱም ፡ በአልጋ ፡ ምክንያት ፡ ከአጼ ፡ ሚናስ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ ቈይተው ፡ ለማልሞ ፡ ላይ ፡ ቃስረው ፡ ሲኖሩ ፡ ፍጻሜያቸው ፡ ሳይታወቅ ፡ በመቅረቱ ፡ ነው ። ያቤቶ ፡ ፋሲል ፡ ግን ፡ የታወቀ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መደፈት ፡ በጽሑፍ ፡ ተዘርዝሮ ፡ ይገኛል ። አቤቶ ፡ ፋሲልም ፡ አቤቶ ፡ ተገክረ ፡ ቃልም ፡ ከአጼ ፡ ሚናስ ፡ ጋራ ፡

ተዋግተው፡ዕድል፡አላገኙም፡ነበር ። ያቤቶ፡ፋሲል፡ልጅ፡ሱንስዮስ፡ማን፡ዕድለኛ፡ሆነው፡አልጋውን፡ወረሱ ።

ከአጼ፡ሱስንዮስ፡የቀጠለው፡የጐንደር፡ቤተ፡መንግሥት፡ዘርፍ፡እስከ፡አጼ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ፡ፈጻሜ፡መንግሥት፡ድርሰ፡ሲኖረጥ፡የሸዋ፡ቤተ፡መንግሥት፡ዘርፍ፡ከአጼ፡ሱስንዮስ፡አጎት፡ከአቤቶ፡ሥላሴ፡ቃል፡ጀምሮ፡እስከሁን፡ደንበኛ፡እርምጃ፡እንደ፡ቀጠለ፡ነው ።

የጐንደርና፡የሸዋ፡ቤተ፡መንግሥት፡የትውልድ፡ሐረግ፡ከአጼ፡ልብነ፡ድንግል፡ጀምሮ፡እስከለንበት፡ዘመን፡ድረስ፡ተዘርዝሮ፡ስለሚገኝ፡አቤቶ፡ሥላሴ፡ቃል፡ታሪክ፡እንዳይዘለል፡ከዚህ፡እንደሚከተለው፡በጭሩ፡እገልጻለሁ ።

አቤቶ፡ሥላሴ፡ቃል ።

አቤቶ፡ሥላሴ፡ቃል፡ከአቤቶ፡ያዕቆብና፡ከበጌምድር፡ባላባት፡ማን፡ከሚወለዱት፡ከመይዘሮ፡ንግሥት፡ዓዜብ፡ተወለዱ ። አቤቶ፡ፋሲልና፡(ገራም፡) አቤቶ፡ተገክረ፡ቃል፡የሚባሉ፡፪፡ወንድማማቾችና፡መይዘሮ፡መለተ፡ማርያም፡የተባሉ፡እጎት፡ነበሩዋቸው ። አቤቶ፡ፋሲል፡ለጐንደር፡ንግሥትና፡ለጐጃም፡መሰፍንት፡የትውልድ፡ርእሰ፡ሐረግ፡እንደመሆናቸው፡መጠን፡ታናሽ፡ወንድማቸውም፡አቤቶ፡ሥላሴ፡ቃል፡ለሸዋ፡ንግሥትና፡መሰፍንት፡የትውልድ፡ርእሰ፡ሐረግ፡ናቸው ።

የዚህም፡የአቤቶ፡ሥላሴ፡ቃልን፡ትውልድ፡መከታተል፡መሥመራን፡ሰይለቅ፡የንጉሥ፡ንግሥትን፡ዙፋንና፡ዘውድ፡ከዳግማዊ፡ምኒልክ፡ጀምሮ፡እስከ፡ንግሥቲት፡ንግሥትነት፡ዘውዲቱ፡ደረሰ፡ከዚያም፡ቀጥሎ፡በንጉሥ፡ሣህለ፡ሥላሴ፡ልጅ፡በወይዘሮ፡ተናኘ፡መርቅ፡በኩል፡የወረደው፡ሐረግ፡ለግርማዊ፡ቀዳማዊ፡አጼ፡ኃይለ፡ሥላሴ፡ደረሰ ።

በአርበኞቹ፡ንግሥትነት፡አባቶቻቸው፡በንአጼ፡ልብነ፡ድንግልና፡በንአጼ፡ገላውዲዮስ፡የደረሰው፡ዕድል፡በግርማዊ፡ቀዳማዊ፡አጼ፡ኃይለ፡ሥላሴ፡ደርሶ፡አይተነዋል፤በታሪክም፡ተመዝግቦ፡ይገኛል ።

ግራኝ፡መሐመድ፡የአጼ፡ልብነ፡ድንግል፡ንጉሣዊ፡ሰውነት፡መንገላታትና፡መከራን፡የማይችል፡መስሎት፡በአነስተኛ፡ግምት፡ስለ፡ገመተው፡ልጅዎን፡ይዳሩልኛና፡እንታረቅ፡ሲል፡የዕርቅ፡ድርድር፡ቢልክባቸው፡ቄራው፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ላንተ፡ልጄን፡ሰጥቼ፡ጦርነቱን፡ከማስቀረት፡በነጠአታችን፡የፈጠረን፡ጌታ፡ቢቀጣን፡ይሻላል፡ብለው፡እንደመለሱትና፡እስከ፡መፈፈሻውም፡ድረስ፡ተጋድለው፡በሰማዕትነት፡እንዳረፉ፤ጀግናው፡ልጃቸው፡አጼ፡ገላውዲዎስም፡የብዙ፡ጊዜ፡ጠላታ



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኦቪ ፡ ኃ.ሰ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ቸውን ፡ ከተበቀኦላቸው ፡ በኋላ ፡ በትውልት ፡ መታደር ፡ አዲስ ፡ ጕልበት፡ ከላቸው ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ መሞታቸውን ፡ ታሪክ ፡ ይመሰክርላቸዋል ።

እንዲሁም ፡ ሙሶሊኒ ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ ከማዘትም ፡ በከፊል ፡ ይልቁ ቁልኝና ፡ እንታረቅ ፡ ሲል ፡ ያቀረበውን ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ፡ አለ ፡ መቀበል ፤



ግርማዊቅ ፡ እቴጌ ፡ መነን ።

አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ለግራኝ ፡ ከሰጡት ፡ መልስ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ በመ
ሆኑ ፡ ይኸንኑ ፡ የጀግንነታቸውን ፡ ተግባር ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ መ-ሶሊኔ ፡ በገዙ፡
ሕዝቡ ፡ እጅ ፡ ሲገደል ፡ ንጉሡም ፡ ከገር ፡ ተሰደ ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ተሰዶ ፡ ሞቶ ፡

ሲቀር ፡ አልጋ ፡ መራሹም ፡ ይኸው ፡ ዕድል ፡ ገጥሞት ፡ ካገር ፡ አገር ፡ እየ ተንከራተተ ፡ ሲኖር ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ መሰናክል ፡ ተመልሰው ፡ በተወደደው ፡ ሕዝባቸው ፡ መካ ከል ፡ ተገኝተው ፡ በጠላት ፡ ተወርሶ ፡ የነበረውን ፡ አገራቸውን ፡ መልሰውና ፡ አቋቁመው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነትና ፡ በእርሳቸውም ፡ ትግል ፡ ያበቡ ትን ፡ መታሰቢያ ፡ ለማቋቋም ፡ በቁ ።

ይህንንም ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሰበኝ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የታ ወቀ ፡ ታሪክና ፡ የታሪክ ፡ ደራሲዎች ፡ ከጻፉት ፡ ያልተለየ ፡ ቢሆን ፡ ይበልጥ ፡ ጉልህ ፡ ሆኖ ፡ ከረጅሙ ፡ ባጭሩ ፡ ተጠቃሎ ፡ ግልጽ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኖ ፡ የተ ፈለገ ፡ እንዲሆንና ፡ ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ እንዲያውቀውና ፡ ለማ ጥናትም ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝለት ፡ በማለት ፡ ነው ።

በንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ የእገሌ ፡ ልጆች ፡ እገሌና ፡ እገሌ ፡ ናቸው ፤ ሌሎ ችም ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ነበሩዋቸው ፡ እያለ ፡ ስማቸው ፡ ሳይገለጽ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

ይህም ፡ አጻጻፍ ፡ ከለማወቅ ፡ የተነሣ ፡ ሳይሆን ፡ እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ ሌላውም ፡ ያውቀዋል ፡ በማለትና ፡ እንዳወቀውም ፡ በመቁጠር ፡ ከታሪክ ፡ ደራሲዎች ፡ ስለሚዘለልና ፡ ቸል ፡ ስለሚባል ፡ ነው ።

በበኩሌም ፡ ለሆነው ፡ ግድፈት ፡ የእንባቢዎቹ ፡ የማረሚያ ፡ ርዳታ ፡ ተገኝቶበት ፡ ለመደፈቱ ፡ በሰፊው ፡ ታርሞ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ተስፋ ፡ በማድ ረግ ፡ ላሁኑ ፡ ጊዚ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እገልግሎት ፡ ተገኝቶበት ፡ ለሕዝቡ ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ አዘጋጀሁ ።

ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የነገሥታቱን ፡ ትውልድ ፡ የሚገልጹት ፡ ጥንታ ውያን ፡ መጻሕፍት ፡ የገለጹትን ፡ ያህል ፡ ለመግለጽና ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ ባይገኝ ፡ ኖረ ፡ አስረጅ ፡ በማጣት ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለመደፈቱ ፡ ኖረ ፡ አስረጅና ፡ ጽሑፍ ፡ ቢገኝ ፡ በሰፊው ፡ እየታረመ ፡ የሚሞላ ፡ መሆኑን ፡ ለእንባቢዎች ፡ እያስገነዘብኩ ፡ ማረሚያዎቹን ፡ በታላቅ ፡ ተስፋ ፡ የምጠባበቅ ፡ መሆኔን ፡ በትሕትና ፡ እገልጻለሁ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸውን ፡ የነገሥታት ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ከሰረዓይ ፡ በኋላ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ሐረግ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ስፍ ራውን ፡ ወሰቆ ፡ እንዲይዝና ፡ ሌላውም ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ ወሰቆ ፡ እንዲያጠናው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ተዘረዘረው ፡ የትውልዱን ፡ ሐረግ ፡ አበረክታለሁ ።